## የዋና ሥራ አስኪያጅ መልዕክት



የመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች ለአንድ አገር ኢኮኖሚ ልማት ከፍተኛ አስተዋፆ አላቸው፡፡ በተለይም ባለሁለት አሃዝ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት በማስመዝገብ ላይ ለሚገኙ እንደ ኢትዮጵያ ላሉ አገሮች ለዜጎች ሰፊ የሥራ ዕድሎችን በመፍጠር ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን በመፍታት ረገድ የሚኖራቸው ሚና የጎላ ነው፡፡ በመሆኑም በአምስቱ ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ውስጥ የኢትዮጵያ መንግስት ለሀገሪቷ የመሠረተ ልማት ግንባታ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ በመንቀሳቀስ ላይ እደሚገኝ  ይታወቃል፡፡ በተለይም መንግስት ለመንገድ ግንባታ ዘርፍ የሰጠው ትኩረት እጅግ ከፍተኛ ሲሆን ለአገር በቀል የኮንስትራክሽን ኩባንያዎች የግንባታ መሣሪያዎችን ከቀረጥ ነፃ እንዲያስገቡ በመፍቀድ፤ የአቅም ግንባታና የእውቀት ሽግግር ፕሮግራሞችን በማመቻቸት ለዘርፉ ዕድገት አስፈላጊውን ድጋፍ እያደረገ እንደሚገኝ እሙን ነው፡፡

ድርጅታችን፣ ገምሹ በየነ ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ፣ ካሉት ሀገር በቀል ኮንስትራክሽን ድርጅቶች ውስጥ ደረጃ 1 ኮንትራክተር ሲሆን፣ መንግስት ባመቻቸው የልማት ፖሊሲ መሰረት በተለያዩ የሀገሪቱ ክልሎች በመንገድ ግንባታ ሥራ ላይ ተሰማርቶ ይገኛል፡፡  ኩባንያው ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ በመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች ላይ ትኩረት በማድረግ ለዘርፉ ዕድገት የበኩሉን አስተዋፆ በማበርከት ላይ ይገኛል፡፡ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው በርካታ ተግዳሮቶቸ ያሉበት ዘርፍ ቢሆንም፣ እስከአሁን ትላልቅ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶችን በሚፈለገው የጥራት ደረጃ አጠናቆ የደንበኞችና የባለድርሻ አካላት ፍላጎትን ባሟላ መልኩ ከኮንትራት ጊዜአቸው ቀደም ብሎ በማስረከብ ለአገልግሎት እንዲበቁ ለማድረግ ችሏል፡፡ በዚህ ረገድ እ.ኤ.አ በ2007 የተጠናቀቀው የድሬደዋ-ደንገጎ-ደወሌ-ቁሉቢ 280 ኪ.ሜ መደበኛ ጥገና ሥራ መንገድ ፕሮጀክት፣ በዚሁ ዓመት (እ.ኤ.አ በ2013) የተጠናቀቀው ማይፀምሪ-ዲማ 76.6 ኪ.ሜ የአስፋልት መንገድ ፕሮጀክት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

በአሁኑ ጊዜም ትላልቅ የአስፓልት መንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶችን ተረክቦ በመሥራት ላይ የሚገኝ ሲሆን አፈጻጸማቸውም በጥሩ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ ኩባንያው እስከአሁን ከ500 በላይ ለሚሆኑ ዜጎች ቋሚ የስራ ዕድል፤ ከ2000 በላይ ለሚሆኑ ሰዎች ደግሞ ጊዜያዊ የሥራ ዕድል የፈጠረ ሲሆን የሰው ኃይል ስብጥሩም እስከ ዶክተሬት ድግሪ ድረስ የትምህርት ደረጃ ያላቸው ባለሙያዎችን ያካተተ ነው፡፡

## Message From The General Manager

አቶ ገምሹ በየነ
ዋና ሥራ አስኪያጅ
Ato Gemshu Beyene, General Manager

*In a country of double digit economic growth record, like our Country, the role of infrastructure development is so enormous. It plays the leading role in the creation of the highest job opportunity for citizens thereby expediting and supporting the socio-economic development of a Country. As part of its multi-faceted effort, the government of Ethiopia has accorded high priority to the country's infrastructure development program in its five year Growth and Transformation Plan (GTP). Especially, the construction of road network throughout the country has received great emphasis through the provision of the necessary support in terms of import of duty free construction machineries, capacity building and knowledge transfer programs to indigenous construction companies.*

*Gemshu Beyene Construction (GEBECON) PLC, is one of the indigenous construction companies focusing and specializing on road construction works. Since its establishment, the Company has been making maximum effort in contributing its fair share in the development of national road infrastructure. Despite the many challenges facing the sector, GEBECON Plc has successfully completed major road construction projects meeting the required quality standards and satisfying the needs of its client and stakeholders. In this regard, the successful completion and handing over of the Diredawa- Dangago-Dewalle -Kulubi 280 k.m routine term maintenance project in 2011 and the Maytsebry-Dima 76.6 k.m Asphalt Road Project in 2013 can be mentioned as key achievements of the company. These projects have been delivered and made ready for the intended use prior to the contract period.*

*Currently, the Company has major Asphalt Road Construction projects on hand with the status of good accomplishment. So far, the Company has created job opportunities for more than 500 permanent and 2,000 temporary employees. The Company's staff mix is so diverse with good educational background ranging up to PhD level.*

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ፈጣን ለውጥ ከሚታይባቸው ዘርፎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ የደንበኞችን ፍላጎት በአርኪ ሁኔታ ለመሟሟላት ከጊዜው ጋር የሚሄድ ቀልጣፋና ውጤታማ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት ግዴታ እየሆነ መጥቷል፡፡ በመሆኑም የኩባንያውን ራዕይና ስትራቴጂ ከወቅቱ የኢኮኖሚ ሁኔታና በዘርፉ ከሚታየው የውድድር ሁኔታ እንዲሁም ከዓለም አቀፍ ነባራዊ ሁኔታዎች አንጻር በየጊዜው መቃኘት አስፈላጊ መሆኑን ማኔጅመንቱ ያምናል፡፡

ስለሆነም ማኔጅመንቱ ኩባንያውን ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር ሥር ነቀል የለውጥ እርምጃዎችን በመውሰድ ላይ ይገኛል፡፡ ከዚህም ውስጥ አንዱና ዋነኛው ISO 9001:2008 የአሠራር ሥርዓትን መዘርጋት ነው፡፡

ለዚህም ስኬት እንዲረዳ ብቃት ያለው የሰው ሀብት ይዞ መገኘት ወሳኝነት አለው፡፡ በዚህ ረገድም ኩባንያው አውደ ጥናቶችን በማዘጋጀት፤ ለሠራተኞቹ ሥልጠናዎችና የሥራ ላይ ልምምድ ፕሮግራሞችን በማመቻቸት የሰው ሀብቱ እውቀትና ክህሎት በየጊዜው እንዲሻሻል በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ የኩባንያውን አመራር ብቃትና ኢንተርፕረነርሸፕ ክህሎት ለማሻሻል ቀጣይነት ያላቸው የአቋም ዳሰሳና የማብቃት እርምጃዎች እየተወሰዱ ናቸው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የዘመናዊ የግንባታ ቴክኖሎጂዎችን፤ የተሻሻሉ የግንባታ መሣሪያዎች አያያዝና ጥገና ሥርዓት ብሎም ዘመናዊ የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ዘዴዎችን ቀስሞ ሥራ ላይ ለማዋል እንዲቻል ኩባንያው በአሁኑ ጊዜ ከፍተኛ ኢንቨስትመንት ወጪ መድቦ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡ በቀጣይ ዓመታትም ከፍተኛ የጥራት ደረጃ ያላቸው የመንገድ ግንባታ አገልግሎቶችን የሚሰጥ ጠንካራ ተቋም ሆኖ እንዲቀጥል አደረጃጀቱንና የአሰራር ስርዓቱን የበለጠ ማሻሻል አስፈላጊ ጉዳይ መሆኑን ምን ጊዜም የማኔጅመንቱ እምነት ነው፡፡

በአሁኑ ጊዜ መንግሥት የአገር በቀል ኩባንያዎችን አቅም በማጎልበት አገሪቷ የምታወጣውን የውጭ ምንዛሪ ለማስቀረት   እያደረገ ያለውን ድጋፍ ኩባንያችን ያደንቃል፡፡ በዚህ ረገድ ቀጣይነት ላለው የካምፓኒው ዕድገትና ለአገርቷ የመንገድ ግንባታ ዘርፍ እድገት ከፍተኛ ድጋፍ ላበረከቱት የግልና መንግስታዊ ተቋማት ሁሉ ኩባንያችን ምስጋናውን ያቀርባል፡፡

ኩባንያው አሁን ያለበት ደረጃ ላይ ሊደርስ የቻለው ሠራተኞቹ ባሳዩት ያላሰለሰ ጥረት እንደሆነ ያምናል፡፡ ለዓላማው ስኬት ማንኛውንም መስዋእትነት ለመክፈል ዝግጁ የሆኑ ጠንካራ ሠራተኞችና የማኔጅመንት አባላት ያሉት በመሆኑ ኩባንያው በዚህ ይኮራል፡፡ ከዚህ የተሻለ ለመሥራትና የበለጠ ውጤት ለማስመዝገብ ብዙ ይጠበቅብናል፡፡ በመሆኑም በቀጣይ የታለሙትን የኩባንያውን ዓላማዎችና ግቦች ለማሳካት የኩባንያው ማኔጅመንትና ሠራተኞች እጅና ጓንት ሆነው እንዲሚሰሩ ሙሉ እምናቴ ነው፡፡ ለወደፊቱ የበለጠ ውጤት እንደምናይ ሙሉ እምነቴ ነው፡፡

*GEBECON PLC has well noted the call for efficient, effective and well established system in the face of complex dynamics driving the construction sector and an increasing pressure towards the provision of the highest quality road construction services.*

*Accordingly  some bold steps have been taken thus far by the management to re-enforce comprehensive change and transformation of the Company, which include the implementation of ISO 9001:2008.*

*Moreover, realizing the glaring need to identify and develop strong human resource base, the Company is spearheading in terms of human resource development  by giving workshop and training programs as well as arranging on the job-training to upgrade the knowledge and skills of its employees. Continuous assessment and development of the leadership capacity of the management is also another important area of engagement to improve the Company's entrepreneurship flair.*

*The company  is also making huge investment in the use of advanced construction technologies and the transfer of advanced equipment management and maintenance system, and modern construction management practices. The management always upholds the importance of making further improvements in the organization and management of the company to ensure that the Company remains strong in the provision of the highest quality road construction services in the years to come.*

*At this point in time, GEBECON Plc fully recognizes the continuous support provided by the government to develop the capacity of indigenous construction companies to enable the Country retain foreign currency drainage. The Company would like to take this great opportunity to thank the many public and private institutions who provided their unwavering support to our company's growth in particular and for the sustainable development of the road construction sector in the country in general.*

*GEBECON Plc is truly honored to have very strong, committed and dedicated management and staff members who are always ready to go extra mile and pay any price in moving it forward.  As the Company is still far to go in order to further achieve more remarkable results, I urge the management and staff members to unite towards achieving the envisaged Company goals and objectives during the years ahead.  The best is yet to come. I thank you.*

## የገበኮን አመሠራረትና ዕድገት

ገምሹ በየነ ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ (ገበኮን) በብር 20 ሚሊዮን ካፒታል እ.ኤ.አ በ2007 በደረጃ 1 ሥራ ተቋራጭነት የተቋቋመ ኩባንያ ነው፡፡ የኩባንያው መነሻ ካፒታል የተገኘው በ1996 ዓ/ም ከተቋቋው የፊንጫአ ፏፏቴ የደረቅ ጭነት ማመላለሻ ድርጅትና የአቶ ገምሹ ባላቤት በሆኑት በወ/ሮ ፀሐይ ወ/ሰንበት በ1997 ከተቋቋመው የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ኪራይ አገልግሎት ነው፡፡ ኩባንያው ከተቋቋመ በአጭር ጊዜ ውስጥ በመንገድ ግንባታ ዘርፍ ከፍተኛ ስኬት በማስመዝገብ ተመራጭ ከሆኑት የአገር በቀል ኩባንያዎች ውስጥ አንዱ ለመሆን በቅቷል፡፡

ኩባንያው በካፒታል፤ በሰው ኃይል፤ በሚይዛቸው የመንገድ ፕሮጀክቶች ደረጃ ከጊዜ ወደ ጊዜ ከፍተኛ እመርታን አሳይቷል፡፡ እ.ኤ.አ በ2012 መጨረሻ ላይ የአጠቃላይ ንብረቱ መጠን ከብር 200 ሚሊዮን በላይ የሚገመት ሲሆን ከፍተኛ የትምህርት ደረጃና የሥራ ልምድ ያላቸው መሃንዲሶችና ድጋፍ ሰጪ ባለሙያዎችን ጨምሮ በድምሩ ከ2500 በላይ ለሚሆኑት ዜጎች የሥራ ዕድልን ፈጥሯል፡፡

በአሁኑ ጊዜ ኩባንያው ዘመኑ ያፈራቸውን የኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂዎችን የሚጠቀም ሲሆን ከ200 በላይ የሚሆኑ የተለያዩ የግንባታ መሣሪያዎች፤ ከባድ መኪናዎችና ተሽከርካሪዎች ባላቤት ነው፡፡ በዋናው መ/ቤትና በየፕሮጀክቱ ለግንባታ መሣሪያዎችና ተሽከርካሪዎች የጥገና አገልግሎት የሚሰጡ የተሟላ ፋሲሊቲዎች ያሉት ዘመናዊ ዎርክሾፖችም አሉት፡፡

ኩባንያው የሥራ አድማሱን በማስፋፋት የአፍሪካ ህብረትና ሌሎች የቀጠና፤ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ድርጅቶች መቀመጫ በሆነች መዲናችን አዲስ አባባ እምብርት ላይ እሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል የተሰኘ ባለአምስት ኮከብ ሆቴል ለመገንባት ዋና ምክንያት ሆኖዋል፡፡



GEBECON in 2008/ገበኮን በ2000 ዓ.ም



## GEBECON Establishment and Historical Development

GEBECON PLC was established as General Contractor (GC) 1 with an initial investment outlay of Birr 20 million in 2007. Although the Company has come a long way before entering into the road construction business, it has evolved rapidly ever since its establishment. It sprouted from Fincha Fafuate Transport PLC and Tsehay WoldeSenbet Construction Machineries & Equipment Leasing Service. Within a short period of its establishment, the Company has managed to register a remarkable and outstanding performance in road construction works and is emerging as one of the best choices in the sector.

It has grown very large (among others) in terms of capital, number of employees, and grade of roads constructed in the country. Consequently, the company's total asset has grown to more than Birr 200 million at the end of 2012. The Company is staffed with qualified engineers and support professionals and has created jobs for over 2,500 citizens.

The company has put in place the state-of-art construction technologies to meet its strategic objectives and goals. Currently, it has more than 200 different construction machineries and equipments including different trucks and vehicles. It has also workshops both at head office and construction sites equipped with the necessary tools to facilitate maintenance activities.

The company is also diversifying its business activities. At the heart of Addis Ababa, which is the seat of African Union and many regional and international organizations including ECA, UN, and various NGOs, the company has become the main reason for the birth of a five star hotel named Elilly International Hotel.



GEBECON in 2012/ገበኮን በ2004 ዓ.ም

# የኩባንያው የበላይ አመራሮች

# Senior Management Staff



ኢንጂነር ግርማ ጉሉማ
ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ
Eng. Girma Guluma, Deputy General Manager

በአገሪቷ እጅግ ስኬታማ የሆነ ኩባንያ አባል በመሆናችን የገበኮን ማኔጅመንት አባላት ከፍተኛ ደስታ ይሰማናል፡፡ ይህንን ስኬት ጠብቀን ለማቆየትና በዓለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂ ሆነን ለመገኘት በየጊዜው ሥራችንን ለማሻሻልና ለማስፋፋት እንተጋለን፡፡

በምንሠራቸው ፕሮጀክቶች ላይ ለሚያጋጥሙ ችግሮች አፋጣኝ መፍትሔ ለመስጠት እንዲቻል ከውጪ አገር ጭምር ብቃት ያላቸው ባለሙያዎችና አስፈላጊ የሆኑ የኮንስትራክሽን ማሽነሪ መለዋወጫዎችን በፍጥነት እናቀርባለን፡፡ በዋና መ/ቤትም ሆነ በየፕሮጀክቱ ያሉት ሠራተኞቻችን በትጋት የሚሠሩ ናቸው፡፡

በማቴሪያል አያያዝ፤በሰው ሀብት፤መሣሪያዎችና ፋይናንስ  አስተዳደር ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረጋችንና  ተገቢ የፕሮጀክት ቁጥጥርና ክትትል ዘዴን መከተላችን ፕሮጀክቶቻችንን በወቅቱ አጠናቀን የደንበኞቻችንን ፍላጎት ለማርካት አስችሎናል፡፡ ለአንድ ፕሮጀክት የተመደበውን በጀት ለፕሮጀክቱ ሥራ ብቻ የምናውል ሲሆን ለፕሮጅክቱ ሥራ የሚያስፈልጉ ግብአቶች በወቅቱ እንዲቀርቡ ለማድረግ ኩባንያው ተግቶ ይሠራል፡፡

የስኬታችን ምሥጢር አንዱ የኩባንያው ዋና ሥራ አስኪያጅና ባላቤት የሚያሳዩት ትጋትና፤በየጊዜው የሚያደርጉት ክትትልና ለሚያጋጥሙ ችግሮች የሚሰጡት አፋጣኝ መፍትሔ ነው፡፡

ያሉብንን አንዳንድ ድክመቶች በመተግበር ላይ በሚገኘው የISO 9001-2008 ሥርዓት አማካይነት እንደምናሻሽላቸው እርግጠኞች ነን፡፡ አመሰግናለሁ፤

*ኢንጂነር ግርማ ጉሉማ በሲቪል ምህንድስና ከአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ የባችለር ድግሪ፤ በኬምስትሪ ከቀድሞው የባህር ዳር ፖሊቴክኒክ ተቋማ አድቫንሲድ ዲፕሎማ አላቸው፡፡ አቶ ግርማ በተለያዩ መ/ቤቶች በተለያዩ የኃለፊነት ደረጃ ከ16 ዓመት በላይ ያገለገሉ ሲሆን ቺፍ ኢንጂነር፤ ፕሮጀክት ዳይሬክተር፤ ፕሮጀክት ማኔጀር፤ኮንስትራክሽን ኢንጂነርና ኦፊስ ኢንጂነር በመሆን ሠርተዋል፡፡*

The management team of GEBCON PLC is happy being the member of one of the best successful construction companies of this country. Year after Year, we are working hard to improve and extend our works while keeping in mind our ultimate goal to see GEBCON PLC being one of the best internationally known construction company.

We give our very best to address the problems and challenges facing projects to the extent of supplying professionals and spare parts from overseas as earlier as possible. Most of our staff members both at project sites and head office level are committed to their assignment.

Generally careful consideration in the management of Material, Labor, Equipment and Finance with appropriate project monitoring and evaluation mechanism resulted in attaining our project plan and satisfying our client demand on time. For instance, the income generated from the works of a given project is merely used for the sole purpose of that project and besides the company is vigilant on issues related to the supply demand by projects.

The owner and the General Manager of the company's commitment, follow up, pragmatic action and solutions on the problems facing each day is one of the secret behind the success of the company, which is very much appreciated. We hope that some of our weakness shall be addressed with the implementation of ISO 9001-2008, which we have already started to do so. Thank you.

*Eng. Girma holds Bachelor Degree in Civil Engineering from AAU Faculty of Technology as well as Advanced Diploma in Chemistry from Bahir Dar Polytechnic Institute. He worked for over 16 years in different organizations with different capacities. He served as Chief Engineer, Project Director, Project Manager, Construction Engineer, & Office Engineer.*



ኢንጂነር ፍቃዱ አበራ
የፕሮጀክቶች ዳይሬክተር
Eng. Fekadu Abera, Construction Director

ከፍተኛ የሥራ ፍላጎትና ብቃት ካላቸው የገበኮን ኩባንያ የበላይ አመራርና ሠራተኞች ጋር በመሥራቴ ከፍተኛ ደስታ ይሰመኛል፡፡ በኩባንያው በቆየሁባቸው ጊዚያት የበላይ አመራሩ በተለይም የኩባንያው ባላቤት በፕሮጀክቶች አፈጻጸም ሂደት የሚያደርጉት የቀን ተቀን ክትትል፤ ለሚቀርብላቸው ጥያቄዎችና ችግሮች የሚሰጡት አፋጣኝ ምላሻና መፍትሔ በጣም ተደንቄለሁ፡፡

ኩባንያው የሚይዛቸው ፕሮጀክቶች ብዛት ከግዜ ወደ ግዜ እየጨመረ በመጣ ቁጥር በአንጻሩ የሚያስፈልገው ክትትል፤ ቁጥጥርና ግምገማ ሥራ ከፍተኛ ይሆናል፡፡ የኮንስትራክሽን መምሪያው ከሌሎች ድጋፍ ሰጪ የሥራ ክፍሎች ጋር በመሆን በአሁኑ ጊዜ ኩባንያው በሚሠራቸው ፕሮጀክቶች ማለትም ዲማ-ፍየል ውሃ፤ መሃል ሜዳ-ዓለም ከተማ፣ አዘዞ-ጎርጎራና የሐረር ባይፓስ  መንገድ ፕሮጀክቶች ላይ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ በመሥራት ላይ ይገኛል፡፡

የዚህ ዓይነቱ ባለራዕይ ኩባንያ አባል በመሆኔ ከፍተኛ ደስታ ይሰመኛል፡፡ ለወደፊቱም ራሴን እንደተቀጣሪ ሠራተኛ ሳይሆን በባላቤትነት ስሜት የበለጠ ውጤት እንዲመዘገብ እሠራለሁ፡፡ ኩባንያው በፍጥነት አድጎ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪና እውቅና ያለው ተቋም እንዲሆን ለማድረግ ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎችና ሠራተኞች ይዞ ማቆየት፤ያሉት ባለሙያዎች አቅም መገንባትና ተገቢ ባለሙያዎችን በተገቢ ቦታ መድበን መሰራት ይጠብቅብናል፡፡

*ኢንጂነር ፍቃዱ አበራ በሲቪል ምህንድስና ከአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ የባችለር ድግሪ አላቸው፡፡ አቶ ፍቃዱ በመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች ዲዛይንና ኳንቲቲ ሳርቬይር፤ ረዳት ረዝዴንት ኢንጂነር እንዲሁም ፕሮጀክት ማኔጀር ሆነው በመሥራት  ከስምንት ዓመት በላይ የሥራ ልምድ አላቸው፡፡*

I am very glad to work along with highly dedicated, committed and qualified GEBECON top management and employees. During my employment at GEBECON PLC, I am highly impressed in the commitment of the top management in realizing the project implementation stages, especially the owner of the Company on his day to day project status follow up, problem solving, and quick response to project issues.

As the construction projects running by the company are increasing from time to time, there is a need for close follow-up, monitoring, and evaluation. The Construction Department together with other supporting Departments is highly working on all projects currently undergoing in the company, namely Maytsebri-Dima road project, Dima-Feyel Weha road project, Mehal Meda-Alemketema Road proect, Azezo-Gorgora Road project, and Harar-By-Pass Road project.

I am very proud of being part of such a visionary company and would like to say I am not feeling like an employee but a partner working to achieve the maximum expected. Nevertheless, in order to build the foundation of this fast growing company and paving the road towards internationally recognized and competitive construction company, we are expected to work much better on retaining qualified and professional employees, develop the capacity of existing professionals and assign the best fit personnel for the required position.

*Eng. Fekadu holds BSC in Civil Engineering from Addis Ababa University. He has  worked for over 8 years in road construction projects involving in design and quantity surveyor, Assistant Resident Engineer, and project management.*



ኢንጂነር ዳንኤል ተስፋ ማሪያም
የኮንስትራክሽን ዕቅድና ኮንትራት አስተዳደር መምሪያ ሥራ አስኪያጅ
Eng. Daniel Tesfamariam, Construction Planning and Contract Administration Department Manager

በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ዘርፍ በየጊዜው ከሚከሰቱ ተለዋዋጭ ሁኔታዎች ጋር አብሮ ለመሄድ እንዲቻል ኩባንያችን ከወሰዳቸው እርምጃዎች ውስጥ አንዱ የኮንስትራክሽን ፕላንና ኮንትራት አስተዳዳር ሥራን በመምሪያ ደረጃ ማዋቀር ነው፡፡

መምሪያው ከተደራጀ አጭር ጊዜ ቢሆንም በፕሮጀክቶች አፈጻጸም የኩባንያውን ምርታማነት የበለጠ ለማሳዳግና ኩባንያው እስከሁን ለገነባው መልካም ስምና ዝና እሴት ለመጨመር የተቻለውን ሁሉ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

ኩባንያው በኢንጂኔሪንግ ሥራዎቹ ልቆ እንዲገኝ ለማድረግ በዘርፉ መልካም ተሞክሮዎችን ለመቅሰም፤ አዳዲስ ሃሳቦችን ለማፍለቅና ተግባራዊ ለማድረግ መምሪያው የበኩሉን ድርሻ ይወጣል፡፡

*ኢንጂነር ደንኤል ተስፋ ማሪያም በሲቪል ምህንድስና ከአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ የባችለር ድግሪ፤ በኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ከረድንግ ዩንቨርሲቲ የማስተርስ ድግሪ አላቸው፡፡ አቶ ደንኤል ስትራክቸራል ኢንጂነር፤ፕሮጀክት ኢንጂነር፤ የኮንስትራክሽን ኮንትራት አስተዳደር ቡድን መሪና ኃላፊ በመሆን በተለያዩ ድርጅቶች ከ12 ዓመት በላይ ሠርተዋል፡፡*

Among the actions taken to move along with the dynamics of the construction Industry, Gemshu Beyene Construction PLC has established independent team at Department level for the Construction Planning and Contract Administration.

Though it is a short period of time since the establishment of the Department, it's endeavoring to meet the Company's growing productivity demand, and also playing an active role in adding values in the already established good reputation of the Company's performance in terms of project accomplishment.

The Department further, by implementing innovative ideas and customizing best practices, will make every effort to enable the Company excel in most aspects of construction engineering practices.

*Eng. Daniel holds BSc in Civil Engineering from Addis Ababa University and MSc in Construction Management from University of Reading. He worked for over 12 years in various capacities including structural engineer, project engineer, construction contract management team leader and head.*



አቶ ቀልቤሳ ኢቲቻ/
የፋይናንስ መምሪያ ሥራ አስኪያጅ/Ato Kalibessa Eticha,
Finance Department Manager

ድርጅታችን ላለፉት ተከታታይ አመታት ትርፋማ የመሆኑ ዋና ምክንያት የድርጅቱ ጠንካራ የፋይናንስ አቅምና አመራር መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህንን የፋይናንስ አቅም ቀጣይነት እንዲኖረው በእቅድና ፕሮግራም በመመራት ለተገቢ አላማ ለማዋል የድርጅቱን የውስጥ ቁጥጥር እና የፋይናንስ ሲስተም የበለጠ ዘመናዊ ለማድረግ እየተሠራ ይገኛል፡፡ በመሆኑም በቀጣይ አመታት ድርጅታችን በሁሉም መስክ በማጠናከር እየተሠራ ባለው ሰፊ የመሠረተ ልማት ግንባታ ውስጥ የራሱን ድርሻ እንደሚወጣ ጽኑ እምነት አለኝ፡፡

በመጨረሻም ሰለቸን ሳይሉ ቀንና ሌሊት ተራራንና ቋጥኝን በማፍረስ የኢኮኖሚ ጀርባ አጥንት የሆነውን መንገድ ለሠሩትና ለሚሰሩት መላ ሠራተኞች ያለኝ ከበሬታና ምስጋና የላቀ ነው፡፡

አቶ ቀልቤሳ በአካውንትንግ እና ፋይናንስ የማስተርስ ዲግሪ ያላቸው ሲሆን በሙያው መስክ በተለያዩ ድርጅቶች ከ25 ዓመት በላይ ሠርተዋል፡፡

Our company was able to operate profitably over the last years. One of the reasons for this success was its strong financial capacity and efficient management system. To sustain this trend we need to further modernize our internal control and financial systems. The department is doing its level best in this regard.

Finally I would like to express my appreciation to our staff who are relentlessly working to contribute their part in the infrastructure development of our country.

*Ato Kelibessa holds Masters Degree in Accounting and Finance and has over 25 years of experience in the field working with different organizations.*



አቶ ዘሪሁን ተመስገን
የሰው ሀብት ሥራ አመራርና አስተዳደር መምሪያ ሥራ አስኪያጅ/Ato Zerihun Temesgen, HR and Administration Department Manager

የሰዉ ሀብት ማንኛዉም ድርጅት ካለዉ ወይም ከሚያፈራዉ ሌሎች ቁሳዊ ሀብቶች ሁሉ የላቀ በመሆኑ ልዩ ትኩረትን ይሻል፡፡ ስለዚህ የሰዉ ሀብት ሥራ አመራር የሙያ ዘርፍ ይህንን ለድርጅት ተከታታይ ዕድገት ወሳኝ የሆነዉን የሰዉ ሀብት ፍላጎት የማቀድ፣ የሟሟላት፣ የማበረታታትና ይዞ የማቆየት ሚና ይኖረዋል፡፡ የድርጅቱ ኮንስትራክሽን ሥራ እንቅስቃሴ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረና እየሰፋ በመምጣቱ አሁን በሥራ ላይ ያለዉን የሰዉ ኃይል በማበረታታትና ይዞ ለማቆየት፣ እንዲሁም አዳዲሶቹን ከገበያ ለመሳብ የሚያስችል እስትራቴጃዊ አቅጣጫ ማመልከቱ ወሳኝነት አለዉ፡፡

ስለዚህ ከድርጅቱ ራዕይ አንጻር የሰዉ ሀብት ሥራ አመራር እስትራቴጂ በመንደፍ በአሁኑ ወቅት የተያዘዉን የለዉጥ ሥራዎች በአጥጋቢ ሁኔታ በማከናወን፣ ድርጅቱ ለወደፊት ተወዳዳሪና ታዋቂ የኮንስትራክሽን ኩባንያ መሆን እንደሚችል እምነቴ የጸና ነዉ፡፡

የሰዉ ሀብት ሥራ አመራር ስትራቴጂዉም ትኩረት ጥራት ያለዉ የሰዉ ሀብት በቅጥር ሟሟላት ይሆናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በሥራ ላይ ያለዉን ሠራተኛ ማበረታታት፣ በስነ ምግባር እንዲታነጽ ማገዝና በሥልጠና ክህሎቱን ማሳደግ እንደሚገባ አምናለሁ፡፡

አቶ ዘሪሁን ከአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ በቢዝነስ ማኔጅመንት የመጀመሪያ ዲግሪ እንዲሁም ከደቡብ አፍሪካ ዩኒቨርሲቲ (University of South Africa) ሁለተኛ ዲግሪ (Masters of Business Leadership-MBL) አግኝተዋል፡፡ በሥራ ዓለም በጠቅላላዉ 24 ዓመት በመንግስትና በግል ድርጅቶች በተለያዩ የኃላፊነት ደረጃዎች አገልግለዋል፡፡ የሠሩባቸዉ ዋና ዋና የሙያ መስኮችም፡- በድርጅት ሥራ አመራርና ሥልጠና፣ በአስተዳደር፣ በአሠራር ሥርዓት ማሻሻያ ጥናት እና ሌሎች ልዩ ልዩ ጥናታዊ ሥራዎችን ያጠቃልላል፡፡

Human resource is the most critical resources of an organization that requires special attention. The human resource management sector has the role of planning, employing, motivating and retaining this critical resource. Considering the growing scope in the construction activities of the company, it becomes imperative to devise a strategy for motivating and retaining the existing human resource and attract new staff from the labor market.

In this regard, we are fully confident that our company is capable of pooling together visionary staff who can speed up the realization of the change program and play major role in making the company more competitive and reputable in the construction industry.

To wards this end, we believe that our human resource strategy should focus on employment of highly qualified staff, motivating and capacitating the existing staff through training as well.

*Ato Zerihun holds BA in Business management from the Addis Ababa University and MBL in Business Leadership from the University of South Africa. He has over 24 years of experience working in different governmental and private organizations in the areas of administration, management, training, system reform and consultancy works.*



አቶ ዋቅጋሪ ሄደታ
የግዥና ንብረት አስተዳደር መምሪያ ሥራ አስኪያጅ/Ato Wagari Hedeta, Procurement and Property Administration Department Manager

አብዛኛው የድርጅቱ ወጪ የዕቃ ግዥ ሲሆን የግዥና ንብረት አስተዳደር መምሪያ ይህን ከፍተኛ ወጪ በመቀነስና የድርጅቱን የፋይናንስ አቅም እንዳይጎዳ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ያደርጋል፡፡ ወደፊት እያደገ የሚመጣውን የአቅርቦት ጥያቄዎችን በአግባቡ ለማስተናገድ የድርጅቱን የግዥ ሥርዓት በዘመናዊ አሰራር በማደራጀት የግዥ ሥራዎችን በጥንቃቄ ማከናወን አስፈላጊ መሆኑን አምናለሁ፡፡

በአጠቃላይ የፕሮጀክቶችን ሥራ በጊዜ ለማጠናቀቅ የዕቃ አቅርቦት ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠው በመሆኑ መምሪያው ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራበት ይገኛል፡፡ ለድርጅቱ ውጤታማነት የኮንስትራክሽን ዕቃዎች አቅርቦት የጀርባ አጥንት በመሆኑ መምሪያችን፣ የግዥና ንብረት አስተዳደር አስፈላጊውን ዕቃ በተፈለገበት ጊዜና ጥራት እንዲሁም በሚፈለገው ብዛት በማቅረብ ከፍተኛ አስተዋፅኦ በማበርከት ላይ ይገኛል፡፡ መምሪያችን የሚገዙትን ልዩ ልዩ የኮንስትራክሽን ዕቃዎች እስከ ፕሮጀክቶች ድረስ በማሰራጨት ለመንገድ ግንባታው ሥራ ጉልህ ሚና እየተጫወተ ይገኛል፡፡

አቶ ዋቅጋሪ ሄደታ በግዥና ንብረት አመራር ዲፕሎማ እንዲሁም በገበያ አስተዳደር የመጀመሪያ ዲግሪ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ንግድ ሥራ ኮሌጅ ያገኙ ሲሆን አሁን የግዥና ንብረት አስተዳደር መምሪያ ሥራ አስኪያጅ ናቸው:: በአጠቃላይ በተለያዩ የኮንስትራክሽን ድርጅቶች ከአስር አመት በላይ በተለያዩ የሥራ መደቦች፣ በግዥ ሰራተኛነት በሰፕላይ ዋና ክፍል ኃላፊነት፣ በፕሮጀክት ድጋፍ ሰጪ ዋ/ክፍል ኃላፊነት ሰርቶዋል፡፡

Cost of materials constitutes the major part in the Company's construction project costs. In view of this consideration, our Department gives due attention to cost reduction. To this end, the Department is committed to put in place modern purchasing system and upgrading the skill of its staff through training in collaboration with the Human Resource and Administration Department.

Timely supply of materials is a critical factor for the completion of project works on time. To this end the department is doing its level best to ensure that the required materials of construction are delivered at the right time, and in the right quality and quantity.

*Ato Wakgari holds Diploma in Purchasing and Property Administration and BA degree from the Addis Ababa University Commercial College in Market Management. He has over ten years of experience with construction companies working as purchasing clerk, head of supply division, and head of support services division.*



አቶ ጌታሁን በቀለ
የመሣሪያዎች መምሪያ ሥራ አስኪያጅ/Ato Getahun Bekele,
Plant and Equipment Department Manager

በዚህ ኩባንያ ገብቶ ለመሥራት ያነሣሣኝ ዋነኛ ምክንያት በአገራችን ካሉ የኮንስትራክሽን ድርጅቶች ለየት የሚያደርገው በመሣሪያዎች አጠቃቀም ላይ ያለው አቋምና ግንዛቤ ነው፡፡ ኩባንያው የሚገለገልባቸው መሣሪያዎች ደረጃቸውን (Standard) የጠበቁ እንዲሆኑ ለጥገናና መለዋወጫ አቅርቦት ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል፡፡

የኩባንያው ሥራ እየተስፋፋ በመጣ ቁጥር የሚይዛቸው መሣሪያዎች ብዛትና አይነት መጨመሩ እሙን በመሆኑ ላሉትና ለወደ ፊቱ በከፍተኛ ወጪ ተገዝተው ለሚመጡ የኮንስትራክሽን ማሽኖች ተገቢው ጥበቃና እንክብካቤ ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል፡፡፡ በመሆኑም የጥገና ክፈሉን ማደራጀት፣ የቴክኒክ ባለሞያዎችን ማሟላት ይጠበቅብናል፡፡ በአንፃሩም እንደአስፈላጊነቱ ከአዳዲስ የቴክኖሎጂ ግኝቶች ጋር ባለሞያዎችን ማሰልጠንና ማዛመድ ትልቁ ኃላፊነት ነው፡፡

በመጨረሻም በአገሪቱ ያለው የመንገድ ኮንስትራክሽን ስራ ተቋራጮች ከጊዜ ወደ ጊዜ እመርታን እያሳዩ በመሆኑ ይህም ኩባንያ አንዱ እንደመሆኑ የወደፊቱ ከፍተኛ ነዋይ ፈሰባቸው ወይም ተከፍሏቸው የሚመጡትን የውጪ ኮንትራክተሮችን መተካት ይችላል የሚል እምነት አለኝ፡፡

*አቶ ጌታሁን በአውቶ መካኒክና በጄነራል መካኒክ በዲፕሎማ አላቸው፡፡ በተለያዩ መንግሥታዊ ተቋማትና የግል ድርጅቶች በሙያ መስኩ ከ30 ዓመት በላይ ሠርተዋል፡፡*

I was inspired to work in GEBECON because of the special attention the company gives to proper utilization and handling of construction machinery and equipment compared to other local construction companies. With the expansion of the companies activities, the size and mix of the construction machinery and equipment will surely increase in the future.

Hence we need to strengthen the maintenance section to meet the maintenance requirement of existing machinery and equipment and those to be newly brought in. in this regard our company is committed to upgrading the skill of its employees and keeping abreast of new technologies.

With its current move, I hope GEBECON will become the best contractor to cover the role currently played by foreign contractors thereby saving the country enormous foreign currency.

*Ato Getahun holds Diploma in Auto and General Mechanic fields. He has over 30 years of experience in the filed working in various governmental and private companies.*



አቶ ጌቱ ጉዲሳ
ተ/የኦዲትና ኢንስፔክሽን አገልግሎት ኃላፊ/Ato Getu Guddisa, A/ Head-Audit & Inspection Service

ኩባንያችን ከጊዜ ወደ ጊዜ ከፍተኛ ዕድገት በማሳየት ያለ ተቋም ሲሆን በቀጣይ ዓመታትም ከዚህ የበለጠ ዕድገት እንደሚኖረው ሙሉ እምነቴ ነው:: እስከሁን ለተመዘገበው ውጤት ሁሉ የበኩላቸውን አስተዋጾ ላበረከቱት ከፍተኛ አድናቆቴን እየገለጽኩ እኔም የኩባንያው ሠራተኛ በመሆኔ ከፍተኛ ደስታ ይሰመኛል፤ ከኩባንያው ጋርም አብሬ ለማደግ ያለኝን ፍላጎት በዚህ አጋጣሚ ለመግለጽ ይወዳለሁ:: ለወደፊቱም ኩባንያው ለሰው ሀብትና መሣሪያዎች አጠቃቀም እንዲሁም ለአቅም ግንባታ ጉዳዮች ትኩረት በማስጠት የበለጠ ተጠቃሚ እንደሚሆን አምናለሁ፡

The company's growth from time to time is impressive and I see a bright future for such growth to double fold in the years to come. I want to express my appreciation to all those who helped the company by devoting the knowledge and time required from them towards its success. I am happy being an employee of the company and wish to grow with it.

I feel that the company can benefit a lot by paying attention to the deployment of human resources and machinery and capacity building programs in the future.

አቶ ጌቱ ጉዲሳ በሀሳብ አያያዝ ዲግር አላቸው:: በተለያዩ መንግሥታዊ ተቋማትና የግል ድርጅቶች በሙያዉ መስክ ከ7 ዓመት በላይ ሠርተዋል::

*Ato Getu holds BA in Accounting and has over Seven years of experience in different organizations.*



*እንጂነር ተስፋዬ አየለ(የውጭ አማካር - የግዥና ኮንትራት አስተዳደር ባለሙያ መሃንዲስ)*/Eng.Tesfaye Ayele (External Advisor - Professional Engineer in Procurement & Contracts Management)

በዛሬው ተለዋዋጭና የውድድር ዓለም ሁኔታ ውስጥ ኩባንያ አቋቁሞ አስማማኝ የሆነ ቢዝነስ መሥራትና የደንበኞችን ፍላጎት ከማርካት ባሻገር ለህብረተሰቡ ዘላቂ ልማት ማስገኘት ከፍተኛ ኃላፊነትና የሙያ ብቃትን የሚጠይቅ ነው:: የገበኮን አመራር መሠረታዊ እሴቶች የተመሠረቱት በዚሁ መርህ ሲሆን ኩባንያው አዳዲስ ክህሎቶችን በየጊዜው በመማርና አሠራሩን በየጊዜው በማሻሻል ለደንበኞች ጥራት ያለው አገልግሎት የመስጠት ባህል አለው:: ኩባንያው በሚከተለው ይህ አቅጣጫና በኮንስትራክሽን ዘርፍ ግንባር ቀደምና ዓለም አቀፍ እውቅና ድርጅት ለመሆን ራዕይ የሰነቀ ሆኖ በማግኘቴ ከፍተኛ ደስታ ይሰመኛል::

ማስታወሻ: *ካላይ የሰጠሁት ሃሰብ የግሌ አስተያየትና የማንንም ተቋም አመለከከት የማይወክል መሆኑ አገልጻለሁ.*

Building and running a sustainable business company, in this competitive and fast changing environment requires high level of responsibility and professionalism that focuses at the satisfaction of not only to our immediate clients but also ensuring sustainable development of the society at large. The values of GEBECON leadership is rooted into these principles and culture of continuous learning and improving technologies of doing business for better quality service delivery to its clients. I feel happy to see the company, GEBECON, moving in this direction and showing success that helps it as a spring board for achieving its long term vision to become an internationally reputable and leading company in the construction sector.

(Disclaimer: This comment is personal and by no means reflects the view of any institution).



የጽህፈት አገልግሎት ቲም/Secretarial Service Team



የኮንስትራክሽንና እንጂነርንግ ቲም/Engineering and Construction Team



የመሣሪያዎች  መምሪያ ቲም/Plant and Equipment Dep't Team



የፋይናንስ  መምሪያ ቲም/Finance Dep't Team



የሰው ሀብት ሥራ አመራርና አስተዳደር መምሪያ ቲም/HR and Administration Dep't Team



የግዥና ንብረት አስተዳደር መምሪያ ቲም/Procurement and Property Administration Dep't Team

# የISO 9001፡2008 ትግበራ በገበኮን

# Implementation of ISO 9001:2008 in GEBECON



ዶ/ር ፋንታ ተስገራ
የኩባንያው አማካሪ
Fanta Tesgera (PhD), Company Advisor

የመሠረተ ልማት አውታሮች ማለትም እንደ መንገድ፤የኤሌክትሪክ ኃይል፤ቴሌኮሙኒኬሼን ወ.ዘ.ተ የመሳሳሰሉት ዘርፎች ዕድገት ለሁሉም አገራዊ ልማቶች መሠረት በመሆናቸው መንግሥት በአምስት ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ እንዲሁም በምዕተ ዓመቱ የልማት ግብ ለዘርፉ ዕድገት ከፍተኛ ትኩረት መስጠቱ ይታወቃል፡፡ በእነዚህ ዘርፎች ላይ ለሚሳተፉ ባለሀብቶች ማበረታቻና ድጋፍ በመስጠት ላይ እንደሚገኝም እሙን ነው፡፡

እያደገ ለመጣው የከተማና ገጠር ነዋሪ ህብረተሰብ የመንገድ ተዳራሽነትን ለማረጋገጥ መንግሥት በመንገድ ልማት ዘርፍ የተለያዩ የአገርቷን ክፍሎች ለማገናኘትና ከአገሪቷ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ፍላጎት አንጻር አስተማማኝ የሆነ መንገድ አቅርቦትና ተዳራሽነትን ለማስፋፋት መንግሥት ብዙ እየሠራ እንደሚገኝ ይታወቃል፡፡

በአሁኑ ጊዜ የመንገድ ግንባታ ዘርፍ በቴክኖሎጂና በግንባታ ጥራት ረገድ ከፍተኛ ለውጥና መሻሻሎች የታዩበት ዘርፍ ስለመሆኑ በዓለም አቀፍ ደረጃ በመገንባት ላይ ከሚገኙ ፕሮጀክቶች ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም አገር በቀል ኩባንያዎች የአሠራር ጥራትና ቅልጥፍናን በፍጥነት በማሻሻል በዘርፉ ያለውን ውድድር መቋቋም ይጠበቅብናል፡፡

አገር በቀል ኩባንያዎች አሁን በመንገድ ግንባታ ዘርፍ ከተፈጠረው አመቺ ሁኔታ ተጠቃሚ የመሆን ዕድላቸው የሚወሰነው ምርታማነትን ለማሳደግ በሚኖራቸው አቅም ላይ ነው፡፡ ይህም ማለት ዘመናዊ የኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂዎች በመጠቀም ፤የውስጥ አቅም በመገንባት፤ የሠራተኛውን ተነሳሽነት በማሳደግና የተሻሉ የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ዘዴዎችን ሥራ ላይ በማዋል ከፍተኛ ጥራት ያለውን መንገድ በተመጣጣኝ ወጪና በጊዜ ገደቡ ሠርተው በማስረከብ የደንበኞችና ባለድርሻ አካላትን ፍላጎት ለማርካት የሚኖራቸው ብቃት ወሳኝነት ይኖረዋል ማለት ነው፡፡

The development of basic infrastructures like road, power, telecommunications, etc are considered as the key driver of all national development initiatives in the Five years Growth and Transformation Plan (GTP) mapped out by the Government of Ethiopia and the Millennium Development Goals (MDGs) set for the country. To this end, the Government has apparently formulated a grand strategy to meet the ever increasing demand for access to basic road infrastructure in rural and urban areas.

Accordingly a massive investment is earmarked for the infrastructure development of the country especially for the road sector to connect different parts of the country, making roads accessible, reliable and sustainable and thereby address the social and economic growth needs of the unfolding population growth in rural and urban areas of the country.

Today, we are witnessing that the road construction sector is highly changing and improving both in terms of technology and the quality of roads being constructed at global level. As the changes in the sector continue to place tremendous pressure on construction companies for efficiency and effectiveness, the level of construction solutions provided by indigenous construction companies need to evolve and develop rapidly to improve the quality of road construction works and withstand the stiff competition in the sector.

The ability of indigenous construction companies to grab the growing opportunities in the sector, thus, largely depends on increased productivity through the deployment of modern construction technologies, the development of in-house capacity and the adoption of best construction management practices, enhancement of employee commitment and satisfaction, and advancement of client and stakeholder expectations via constructing high quality roads at reasonable cost and within the contract period.

ይህንን ሁኔታ በመገንዘብ ገምሹ በየነ ኮንስትራክሽን ኩባንያ የበላይ አመራር በኩባንያው አደረጃጀትና ማኔጅመንት እንዲሁም አቅም ግንባታ ረገድ መሠረታዊ ለውጦችን ለማምጣት የላቀ ጥራት ያለው የመንገድ ግንባታ አገልግሎት ለመስጠት ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

የኩባንያውን የቴክኒክና የማኔጅመንት ብቃት በማሳደግ ለላቀ ድርጅታዊ አሠራር ሥርዓት መሠረት ለመጣል እንዲቻል የድርጅቱ ማኔጅመንት የISO 9001: 2008 ጨምሮ ሁሉን አቀፍ ድርጅታዊ ለውጥ ፕሮግራሞችን ዘርግቷል፡፡ የለውጥ ፕሮግራሙ በርካታ ጉዳዮችን የሚዳስስ ሲሆን በዋናነት የኩባንያውን አደረጃጀት (ድርጅታዊ መዋቅርና ማኔጅመት) መፈተሸ፡ የጥራት አስተዳደር፤ የሀብት አጠቃቀም፤የአመራር ጥራትና የቢዝነስ ስትራቴጂን ያካትታል፡፡ የለውጥ ፕሮግራሙ ዋና ዋና ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፤

- የኩባንያውን ችግሮች ለይቶ ለማወቅና የመፍትሔ እርምጃዎችን ለመቀየስ፤
- በኮንስትራክሽን ዘርፍ የሚያጋጥሙትን ችግሮች ለመቋቋም የውስጥ አቅምን መገንባት፤
- የደንበኛ አገልግሎት፤የሠራተኛውን ድህንነትና የኩባንያውን መልካም ስም የበለጠ ለማሻሻልና ለማሳደግ፤
- ለኩባንያው ወደ ፊት ዕድገት ቀጣይነት ያለው መሠረት ለመጣል ናቸው፡፡

የለውጥ ፕሮግራሙን ተግባራዊ በማድረግና ከላይ የተጠቀሱትን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ እንዲቻል በዋና መ/ቤትና በየፕሮጀክቱ የተለያዩ ሥልጠናዎች እንዲሰጡና አውደ ጥናቶች እንዲካሄዱ ተደርገዋል፡፡ በእነዚህ ሥልጣናዎችና አውደ ጥናቶች አማካይነት ኩባንያው ችግሮችንና የስትራቴጂ ጉዳዮችን በመለየት ብሎም የለውጥ ፕሮግራሞቹን በመተግበር የታቀደውን ድርጅታዊ ለውጥ ለማምጣት የድርጊት መርሃ ግብር ለመንደፍ ችሏል፡፡

በዚሁ መሠረት በአሁኑ ጊዜ የኩባንያውን አሠራር ሥርዓት ዶክመንት የማድረጉና የማደራጀቱ ሥራ የተጠናቀቀ ሲሆን የ ISO 9001: 2008 ሥርዓት ትግበራን የአሠራር ጥራት ማረጋገጫ ሠርቲፊኬት ለማግኘት በሂደት ላይ ነው፡፡ በትግባራው ሂደት እገዛ የሚያደርግ ኮንሳልታንት ኩባንያው ቀጥሮ በማሠራት ላይ ይገኛል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የኩባንያውን አሠራርና ፕሮጀክት ማኔጀመንት ዘዴዎቹን ዘመናዊ ለማድረግ የተለያዩ የአሠራር ማሻሻያ ጥናቶች ተካሄደዋል፡፡

> Consider how hard it is to change yourself and you will understand what little chance you have in trying to change others (Jacob M. Braude)

In recognition of the foregoing realities, the top management of Gemshu Beyene Construction (GEBECON) Plc is committed to making further improvements in the organization and management of the company and the development of stronger in-house capabilities to ensure that the company remains strong in the provision of the highest quality road construction services to the client within the sector.

To provide the foundation for operational and organizational excellence through greater technical and managerial ability, the top management has initiated a comprehensive organization-wide change program that encompasses the implementation of ISO 9001: 2008 Quality Management Systems (QMS) within the company. The initiative has taken on a broad range of issues, which among others include an assessment of the company's underlying structure (organization and management), quality management approach, utilization of company resources, leadership quality, and business strategies. The major objectives of the change program include the following:

- Identify and understand organizational problems and streamline operations
- Develop internal capability to respond to challenges posed by the sector
- Improve and develop client service, employee welfare, and company goodwill, and
- Provide a strong base for company's sustainable growth in the long-run.

In a move towards the fulfillment of these objectives, various trainings and workshops were conducted both at head office and construction site to create the roadmap through which the change program is fulfilled and realized. Based on the trainings and workshops conducted, the company has identified problem areas, major strategic issues, the action plan and the framework to carry out the envisaged change program/transformation within the company.

Currently, system documentation and development was completed, and the implementation of ISO 9001: 2008 Quality Management System (QMS) leading towards ISO certification is started within the Company. In this regard, the Company hired consultants to assist in the implementation and certification of ISO 9001:2008. In addition, various system improvement studies have been conducted in order to modernize company operations and project management practices.

የለውጥ ሂደቱን ለማሳለጥ እንዲቻል ዓላማ አስፈጻሚ የሥራ ሂደቶችን (ኮንስትራክሽን ኢንጂነሪንግና ኮንስትራክሽን ማኔጅመንት) ከድጋፍ ሰጪ አገልግሎቶች ጋር የሚያቀናጅ አዲስ ድርጅታዊ መዋቅር ተዘርግቷል፡፡ በአዲሱ መዋቅር መሠረት የተግባራት ዝርዝር (functional descriptions) የማዘጋጀቱና እና የሰው ኃይል ፍላጎት የመለየቱ ሥራ ተጠናቋል፡፡ የአሠራር መመሪያዎችን መቅረጽ፣ የሥራ መዘርዘርና ተፈላጊ ትምህርትና ሥራ ልምድ (job specification and description) እንዲሁም የኩባንያው የደመወዝ ሥርዓት የመዘርጋቱ ሥራ እየተካሄደ ይገኛል፡፡ የለውጥ ፕሮግራሞቹ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ሲደረጉ የኩባንያውን አሠራርና አፈጻጸም ከማሻሻል ባሻገር ለደንበኞች ከፍተኛ እሴት ለመፍጠር ያስችላሉ ተብሎ ይታመናል፡፡

በዚህ ረገድ ኩባንያው ቀጣይነት ያለው ለውጥን ባህሉ በማድረግ በኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ዘርፍ  አዳዲስ ሃሳቦችን ለማፍላቅና ዘመናዊ  አሠራሮችን ለመጠቀም ፋና ወጊ ሆኖ ለመቀጠል ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል፡፡

As part of the change process, a new organizational set-up that integrates core processes (construction engineering and construction management) with support functions was put in place. In line with this, functional descriptions and manpower requirement definitions were completed. The development of different working manuals, job specification and description, and company salary structure are in the pipeline for implementation. Many of the changes when fully implemented are believed to boost company capacity and performance in order to create maximum value for the client and position the company into a major player in the construction sector.

GEBECON Plc, as a young and growing company, continues to attach importance to the constant quest for change as its founding culture, reflecting a pioneering spirit for innovation and modern construction management practices in the years to come.



ማይፀምሪ-ዲማ በግንባታ ላይ/Mytsebri -Dima While Under Construction

The way the arrow hits the target is more essential than the way it is shot; the way you listen is more essential than the way you talk. Anyone can talk but understanding takes skill (Anonymous)

ገምሹ በየነ ኮንስትራክሽን ከሚገነባቸው የመንገድ ሥራዎች አንዱ የሆነው የማይፀምሪ-ዲማ ፕሮጀክት ግንቦት 09, 2005 ዓ.ም ተመርቆ ለአገልግሎት ክፍት ተደርጓል፡፡በምረቃ ሥርዓቱ ላይ የተገኙት የትግራይ ክልል መስተዳድር አቶ ዓባይ ወልዱ፣ የትራንስፖርት መገናኛ ሚንስትሩ አቶ ድሪባ ኩማና አቶ ዛይድ ወ/ገብርኤል የኢትዮጲያ መንገዶች ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ናቸው፡፡

መንገዱ ከ 519 ሚሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጭ የተገነባና 76.6 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው ሲሆን ከተያዘለት የግንባታ ግዜ ቀድሞ የተጠናቀቀ መንገድ ነው፡፡

Maytsebry-Dima Project is 76.6 km road project constructed with a total outlay of Birr 519 million. GEBCON PLC completed construction of the project ahead of the contract time and the project was inaugurated on 17 May 2013. The inauguration ceremony was attended by guests of honors including H.E Ato Abay Woldu, President of the Tigray Regional Government, H.E Ato Diriba Kuma, Minister of Transport and Ato Zeid W/Gebriel, Director General of the Ethiopian Roads Authority as well as local government officials and the community.





*ክቡር አቶ አባይ ወልዱና ክቡር አቶ ድሪባ ኩማ መንገዱን ሲመርቁ/Guests of Honors H.E Ato Abay Woldu and H.E Ato Diriba Kuma While Cutting the Ribbon During the Inauguration Ceremony*



የአስፋልት ስራ የማይፀምሪ-ዲማ ፕሮጀክት /Asphalt Surfacing Work, Maytsebry-Dima Road Project

ትግራይ ከዛሬ 21 ዓመት በፊት በርካታ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር የነበሩበት ክልል ናት፡፡ ይሁንና መንግስት ባደረገው ጥረት አብዛኛው ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ደረጃ በደረጃ እየተቀረፉ መጥተዋል፡፡ ለምሣሌ በመንገዱ ዘርፍ ብንመለከት በፌደራልና በክልል እንዲሁም በቅርቡ የተጀመረው የዩራፕ ፕሮግራም ጨምሮ በአስር ሺህዎች የሚቆጠሩ መንገዶች ባለቤት ሆናለች፡፡ በክልላችን በርካታ የፌደራል መንግስት በጀት የሚገነቡ የመንገድ ፕሮጀክቶች ይገኛሉ አንዳንድ የአገር ውስጥና የውጭ ሀገር ኮንትራክተሮች ፕሮጀክቶቹ በግዜ የመጨረስ ችግር ሲያጋጥማቸው ይታያል፡፡ ዛሬ የተመረቀው የማይይፀምሪ-ዲማ መንገድ ፕሮጀክት ግን ከዚህ ለየት ያለ ነው፡፡ በዚህ አጋጣሚ መንገዱን የሰራው ገምሹ በየነ ኮንስትራክሽንን ማመስገን እወዳለሁ፡፡ ሌሎች ኮንትራክተሮችም ከዚህ ልምድ ቢወስድ ለድርጅታቸው እና ለሕብረተሰባቸው ይጠቅማሉ ብዬ አምናለሁ፡፡



ክቡር አቶ አባይ ወልዱ የትግራይ ብ/ክ/መ ፕሬዝደንት በምረቃው ላይ ካደረጉት ንግግር የተወሰደ/ Excerpts Taken from the Speech of H.E. Ato Abay Woldu, Tigray Regional Government President

The Tigray Region is one of the regions with various types of socio-economic problems some 21 years ago. These problems are gradually being solved thanks to the effort of our government. For instance today we had road networks in tens of thousands of kms owing to the special attention given to road development at regional and federal levels including the URRAP. There are a number of road projects in our region being financed by the Federal Government budget. A number of local and international contractors had the problem of completing projects as per schedule. But the Maytsebri- Dima road project which is inaugurated today is exceptional in this regard. Hence I would like to thank Gemshu Beyene Construction PLC, contractor of the project for their exceptional performance. I hope that other contractors can benefit themselves and our country if they follow suit.

መንግስት ላለፉት 13 ዓመት የመንገድ ዘርፍ ልማት ፕግራሞች በመገምገምና መነሻ በማድረግ የእድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጋር በሚጣጣም መልኩ የአራተኛው የመንገድ ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ቀርጾ ከፍተኛ እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል፡፡ በዚህም የሁሉን አቀፍ የገጠር መንገድ ተደራሽነት ፕሮግራምን (URRAP) ጨምሮ አጠቃላይ የአገሪቱን የመንገድ ሽፋን በ2007 መጨረሻ ወደ 136,044 ኪ.ሜ ለማድረስ በቁርጠኝነት እየሰራ የሚገኝ ሲሆን ዛሬ የተመረቀው የማይጸምሪ-ዲማ-ፍየል ውሃ -አቢአዲ-ሐውዜን -ፍሬወይኒ የመንገድ ፕሮጀክት የመጀመሪያ ክፍል የሆነው የማይጸምሪ- ዲማ 76.6 ኪ.ሜ አስፋልት መንገድ መንግስት በሶስተኛው የመንገድ ዘርፍ ልማት ካካተታቸው ፕሮጀክቶች አንዱ ሲሆን የዚሁ ጥረት መገለጫ ነው፡፡



ክቡር አቶ ድሪባ ኩማ
የትራንስፖርት ሚኒስትር በምረቃው ላይ ካደረጉት ንግግር የተወሰደ/Excerpts taken from the Speech of H.E. Ato Diriba Kuma, Minister of Transport

*The Governemt launched the Fourth Phase Road Sector Development Program after duly evaluating the performance in the road sector development over the last 13 years and considering the targets set in the Growth and Transformation Plan. Accordingly various activities are being under way including the URRAP to increase road accessibility coverage of the country to 136.044 km by 2007 E.C. The Maytsebri – Dima Road project inaugurated to day is the first part of Maytsebri – Dima- Feyel Wuha-Abahadi-Hauzen-Frewoni road projects under the third phase of the Road Sector Development Program.*




የተመረቀው የአስፋልት መንገድ ክፍል/
Completed Asphalt Section

ባለፉት ዓመታት የአገራችንን የመንገድ መሰረተ ልማት እምርታዊ ለውጥ እያሳየ የመጣ ሲሆን በክልል ትግራይም በነዚህ ጊዜያቶች ከ 600 ኪ.ሜ በላይ መንገዶች ደረጃቸው ተሻሽሏል፤ በአዳዲስ መልክም ተገንብተዋል፡፡ ዛሬ የሚመረቀው የማይፀምሪ-ዲማ መንገድ ፕሮጀክትን ጨምሮ በቅርቡ የግንባታ ሂደታቸው የሚጠናቀቁና በግንባታ ላይ የሚገኙ የመንገድ ፕሮጀክቶችን ሙሉ በሙሉ ሲጠናቀቁ የክልሉ የመንገድ አውታር ተደራሽነት ክፍተኛ ደረጃ ላይ እንደሚደርስና አገሪቱም የምትከተለው አንድ የኢኮኖሚ እና የፖለቲካ ማሕበረሰብ የመፍጠር ሂደት እውን ለማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡



አቶ ዘይድ ወ/ገብርኤል
የኢመባ ዋና ዳይሬክተር
ካደረጉት ንግግር የተወሰደ/Excerpts Taken from the Speech of Ato Zaid W/Gebriel, ERA General Director

*There was rapid change in the development of road infrastructure in our country over the last years. More than 600 km of roads have been newly constructed or upgraded in Tigray Region over the last years. The Maytsebri- Dima road project inaugurated today and others in the pipe line which are soon to be competed in the immediate future are expected to significantly increase road accessibility in the Region thereby facilitating the socio-economic development envisaged for the nation as a whole.*

ይህ የመንገድ ፕሮጀክት ከኢትዮጲያ መንገዶች ባለስልጣን ወሰደን ወደ ስራ ስንገባ የነበረው ትልቁ ስጋታችን ፕሮጀክቱ ከመሀል አገር እጅግ የራቀ መሆኑና አካባቢው ለሰራተኞቻችን እና ለተቋራጩ አዲስ መሆኑ ነው፡፡ ይሁንና ገና ከጅምሩ ከወረዳው እና ከአካባቢው ማሕበረሰብ በተፈጠረው ጥሩ መግባባት እና የመደጋገፍ መንፈስ ስራችን እጅግ ባልጠበቅነው ሁኔታ በተቀላጠፈ መልኩ ሠርተን እነሆ ዛሬ ለዚህ ለደመቀና ላማረ የማይጸምሪ- ዲማ መንገድ ፕሮጀክት ምረቃ ደርሰናል፡፡ እኔ ለአካባቢው ሕብረተሰብና ለመስተዳድር አካላት ያለኝ ክብር ከፍ ያለ ነው፡፡ ትብብራችን በዚህ ከቀጠለ ከዲማ-ፍየል ውሃ እየተገነባ ያለው ሁለተኛው ፕሮጀክት ልክ በዚሁ መልክ አጠናቅቀን እንደምናስረክብ እምነቴ ነው፡፡



አቶ ገምሹ በየነ
ዋና ሥራ አስኪያጂ
ግቤኮን/ሥራ ተቋራጩ ካደረጉት ንግግር የተወሰደ/Excerpts Taken from the Speech of Ato Gemshu Beyene, GEBECON General Manager

*We had concerns when we commenced construction of this project since the project site is far away from the center of the country and new to our company and our employees. However, thanks to the cooperation and harmonious relation created between the company and the Woreda Administration and the local community right from the very beginning, it was possible to facilitate the completion of the project and inaugurate in such a way. In this regard I would like to thank the local community and the government organs for their full support and cooperation. I am fully confident that we will be able to complete in a similar manner the second phase of the project, Dima- Feyel Wuha road, by maintaining our cooperation.*



*በሚረቃ ወቅት የተወሰደ ፎቶ Photo/Taken During the Inauguration*

በፕሮጀክቱ ግንባታ እንዳሳየነው ሁሉ አሁንም መንገዱ ለረጅም ጊዜ እንዲያገለግል እና ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን የአካባቢው ነዋሪ ሕብረተሰብ መንገዱን በንቃት እንዲጠበቅ አስፈላጊ የሚባለውን ሁሉ እናደርጋለን፡፡ የመንገዱ ዋነኛ ተጠቃሚ ሕብረተሰቡ ነውና፡፡



አቶ ሲሳይ ታረቀ
በትግራይ ሰሜናዊ ምዕራብ ዞን የፀለምቲ ወረዳ ዋና አስተዳደሪ ካደረጉት ንግግር የተወሰደ/ Excerpts Taken from the Speech of Ato Sisay Tareke, the Head of Tselmeti Woreda of North-West Tigray Regional Government

*We believe that the local community is the major beneficiary of this road. Hence we will take all the necessary steps to ensure that the community will actively participate in maintaining the safety of the road similar to the participation it has shown during its construction.*

መንግስት ላለፉት 15 ዓመታት የተለያዩ መርሃ ግብሮችን በመቅረጽ በርካታ የአገራችንን አካባቢዎች የልማት ኮሪደሮች በኣዳዲስ መንገዶች ተዳራሽ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ ይህ ዛሬ የሚመረቀው የማይጸምሪ-ዲማ-ፊየል ውሃ-አቢአዲ-ሐውዜን-ፍሬወይኒ መንገድ ፕሮጀክት የመጀመሪያ ክፍል የሆነው የማይፀምሪ-ደማ መንገድ ፕሮጀክትም አዳዲስ የልማት ኮሪደሮች የሚያገናኙ መንገዶች አንዱ ነው፡፡



አቶ ሳምሶን ወንድሙ
የኢመባ ኮሚኒኬሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ካደረጉት ንግግር የተወሰደ/ Excerpts Taken from the Speech of Ato Samson Wondimu, ERA Communication Directorate Director

The Government has formulated various programs over the last 15 years aimed at increasing access to new roads for many development corridors in different parts of our country. The *Maitsemeri – Dima inaugurated today is part of the Maytsebri – Dima- Feyelwuha-Abahadi-Hauzen-Frewoni envisaged to connect new development corridors in the area.*

ይህ ፕሮጀክት 76.6 ኪ.ሜ ርቀት የሚረዝም እና ከ 515 ሚሊዮን ብር በላይ ወጭ የተደረገበት ሲሆን እያንዳንዱን የኢንጅነሪንግ ሥራ በቅርበት በትኩረት በመከታተል ፕሮጀክቱ ጥራቱን በጠበቀ መልኩና በተቀመጠለት እስታንዳርድ መሰረት ተጠናቆ እንሆ ዛሬ ለምረቃ ደርሷል ለዚህም ኮንትራክተሩ ያሳየው ለሌሎች ኮንትራክተሮች አርኣያና ተሞክሮ የሚሆን የስራ አፈጻጸም በዚህ አጋጣሚ ማመስገን እወዳለሁ፡፡



*እንጅነር አበባው አበበ*
*የየረር ኮንሳልትግ እንጅነርስ ተጠር መሃንድስ ካደረጉት ንግግር የተወሰደ/Excerpts Taken from the Speech of Engineer Abebaw Abebe, Yerer Consulting Engineers Resident Engineer*

*The project involves construction of 76 km concrete asphalt road with total outlay of Birr 515 million. There was close follow up on every engineering works of the project to ensure that the required quality standards were adhered to in the course of the construction works. The project which is to be inaugurated today is completed in conformity with the set quality standards. I hence would like to thank the contractor for the extraordinary and exemplary performance in the accomplishment of this project*

## የገበኮን መንገድ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ደረጃ

ገበኮን ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ በመንገድ ግንባታ ዘርፍ የተሰማራ ሲሆን በዘርፉ ያለው ተሳትፎ ከጊዜ ወደ ጊዜ በማደግ ላይ ይገኛል፡፡ ቀጠሎ ያለው ሠንጠረዥ የኩባንያውን ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ደረጃ ያመለክታል፡፡

## Execution of Road Construction Projects

GEBECON has been engaged in road construction since its establishment, and from time to time its participation in the market increases at a satisfactory rate. The following table indicates the project size in value, time of commencement and status of projects.

| ተ.ቁ . | **የፕሮጀክቱ ስም/ Name of Projects** | **የተጀመረበት ጊዜ እ.ኤ.አ/ Commencement Date** | **ያለበት ደረጃ /Status** |
|---|---|---|---|
| 1 | የደንጋጎ መንገድ መደበኛ ጥገና (Dengego Section Routine Term Maintenance Road) | ኖቬምበር 1 ቀን 2007 (1-Nov-2007) | የተጠናቀቀ (ከተያዘለት ጊዜ ቀደም ብሎ) |
| 2 | የማይጸብሪ-ዲማ አስፖልት መንገድ ፕሮጀክት (Maytsebri - Dima Asphalt Road Construction Project) | ሜይ 15 ቀን 2009 15-May-2009 | የተጠናቀቀ (ከተያዘለት ጊዜ ቀደም ብሎ) |
| 3 | ዲማ -ፍያል ውሃ አስፓልት መንገድ ፕሮጀክት (Dima - Fiyel Wuha: Asphalt Road Construction Project) | ኦገስት 31 ቀን 2011 (31-Aug2011) | በግንባታ ላይ (ከተያዘለት ጊዜ ቀደም ብሎ) |
| 5 | የአዘዞ-ጎርጎራ መንገድ ማሻሻያ ፕሮጀክት (Azezo - Gorgora road upgrading project). | ፌብሮዋሪ 27 ቀን 2013 (27-Feb2013 ) | በግንባታ ላይ (በዕቅዱ መሠረት) |
| 6 | የሐረር ባይፓስ መንገድ ፕሮጀክት. (Harar By-pass road Construction Project ) | | በዝግጅት ደረጃ (In Mobilization Period ) |
| 4 | የመሐል ሜዳ ዓለም ከተማ መንገድ ፕሮጀክት (Mehalmeda-Alemketema road construction project) | ፌብሮዋሪ 25 ቀን 2013 (25-Feb2013) | በግንባታ ላይ (በዕቅዱ መሠረት) |

- The master of road is junction where a lot of vehicles shake themselves. (FRANCE)
- Thought and road are the same, they have starting point but, no ending point. (AUSTRALIAN)

የመንገድ ፕሮጀክቶቹ መጠን በመንገድ ርዝማትና ዋጋ ቀጥሎ ባሉት ምስሎች እንደተመለከተ ነው፡፡ ከምስሉ ለመረዳት እንደሚቻለው በቅርቡ የተጀመሩት የመንገድ ፕሮጅክቶች በርዝማት አነስ ያሉ ቢሆንም በዋጋቸው ከፍ ያሉ ናቸው፡፡ ይህም የፕሮጀክቶቹን ውስብስብነት የሚያመለክት ነው፡፡

The following graph shows project size in length versus project value. Though the length of recent projects is decreasing, the increase in their value is followed by the increase in the complexity of the projects.




- The road to success is always under construction. Lily Tomlin
- The whole difference between construction and creation is exactly this: that a thing constructed can only be loved after it is constructed; but a thing created is loved before it exists. Charles Dickens
- In the pregnancy process I have come to realize how much of the burden is on the female partner. She's got a construction zone going on in her belly. Al Roker

ባለፉት ሰባት ዓመታት ኩባንያው በድምሩ ስድስት የመንገድ ፕሮጀክቶችን ለመሥራት ውል የተፈራርሟል፡፡ ከዚህ ውስጥ ሁለቱ የተጠናቀቁ ሲሆን የተቀሩት በግንባታ ላይ ናቸው፡ አፈጻጸማቸውም በመልካም ሂዳት ላይ ይገኛል፡፡




In the last seven years the Company entered in a contract agreement for construction of six projects, out of which 2 of them are completed and the others are under construction with good progress.




ምስሉ የሚያሳየው የፕሮጀክቱ ውስብስብነት ደረጃ ሲሆን ይህም የተገለጸው በዋና ዋና ሥራዎች ማለትም በቁፋሮ፤ በመሠረት ዝርጋታና በአስፋልት መንጠፍ ሥራዎች ነው፡፡

In the above chart, the project complexity is expressed in terms of major activities, like Earthwork, Structure and Pavement.

## ገበኮን የአጋርነት  ስምምነት ተፈራረመ

ገበኮን ከሚያተኩርባቸው ስትራቴጂያዊ ዓላማዎችና ግቦች ውስጥ አንዱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂ ከሆኑ የኮንስትራክሽን ኩባንያዎች ጋር አጋርነት መፍጠር ነው፡፡ በዚህ ረገድ ገበኮን ኃ/የተ.የግል ኩባንያ የመጀመሪያውን ታሪካዊ እርምጃ በመውሰድ ፍንዲሊንግ ኢንኪ (Findling, Inc) ከተሰኘው ዓለም አቀፍ የኢንጂነሪግና ኮንስትራክሽን ኩባንያ ጋር በመንገድ ዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ተባብሮ ለመሥራት የመግባቢያ ሰነድ ፈርሟል፡፡

ፍንዲሊንግ ኢንኪ (Findling, Inc) ተቀማጨነቱ አሜሪካን አገር ሜሪላንድ ሲሆን በሲቪል ምህንድስናው ዘርፍ በተለይም በጂኦ ቴክኒካል፤በኮንስትራክሽን ማኔጅመንትና ኢንቫይሮሜንታል ኢንጂነሪንግ በዓለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂ ኩባንያ ነው፡፡ በእነዚህ መስኮች ለሚከናወኑ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ሥራዎች ኩባንያው ዘመናዊና ወጪ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን የማጋራት አቅም አለው፡፡

ሁለቱም ኩባንያዎች በሲቪል ኢንጂኔሪንግና ኮንስትራክሽን ዘርፍ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ረገድ በጋራ ለመሥራት ከፍተኛ ፍላጎት አላቸው፡፡ በዚሁ መሠረት ፍንዲሊንግ ኢንኪ (Findling, Inc) ከአገራችን የአፈር ሁኔታና የመልክአ ምድር አቀማመጥ ጋር ተስማሚ የሆነ የቁፋሮ፤ የአፈር አያያዝና በመስክ ላይ የግንባታ ማቴሪያሎች ጥራት ፍተሻ ዘዴ እና በመንገድ ዲዛይን ሥራ የAASHTO ስታንዳርድ አጠቃቀምን ጨምሮ ሌሎች ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በማጋራትና ለገበኮን ባለሙያዎች የቴክኒክ ሥልጠናዎችን በመስጠት በትብብር የሚሠራ ይሆናል፡፡

ገገበኮን በመንገድ ኢንጂኔሪንግ ዲዛይንና ኮንስትራክሽን ሥራ የተሰማሩ ሌሎች ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች ጋርም በአጋርነት ለመሥራት ጥረቱን ይቀጥላል፡፡ ይህም በርካታ ጠቀሜታዎች ያሉት ሲሆን ፤

- የቴክኖሎጂና የእውቀት ሽግግር በማስገኘት የአገር ውስጥ አቅምና ብቃትን ለማዳበር የሚኖረው አስተዋጾ የጎላ መሆኑ፤
- በዓለም አቀፍ ጨረታዎች ላይ በብቃት በመወዳደር ገበኮን በሚኖረው ድርሻ የውጪ ምንዛሪን ማዳን፤
- አቅምን የበለጠ በመገንባት በሂደት በሌሎች አገሮች በመወዳደር ለአገሪቷ የውጭ ምንዛሪ ማስገኘት  ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

- Be patient like road, no one knows what tomorrow brings. (GERMANY)
- Zigzag road kill time and money but, straight road saves life. (ISRAEL)

## International Partnership Agreement Signed

As part of its strategic objectives and goals, Gemshu Beyene Construction (GEBECON) PLC has taken the first historic move in establishing partnership with an internationally recognized construction consultant residing in the United States of America (USA).

GEBECON PLC very recently signed a Memorandum of Understanding (MoU) with Findling, Inc, a Maryland, USA Corporation to work together in the area of road construction and design work.  Findling is a USA based Engineering and Construction firm that specializes in Civil Engineering, especially geotechnical, construction management and environmental engineering. It provides the state of the art and innovative technology, and cost effective solutions for horizontal construction projects.

Both GEBECON and Findling are interested to work together in the area of current technologies in the field of Civil Engineering Design and Construction. The technologies provided by Findling could include ground improvement and ground modification techniques (such as handling swelling soils that are prevalent in Ethiopia); soft soils that may require surcharging and wick drains; slope stability analysis and phased construction; deign of under-drains; field testing of construction materials; design of pavements using the latest AASHTO methods, and technical trainings.

GEBECON continues to forge partnership with prominent companies engaging in road engineering design and construction, both local and overseas. This will have a number of benefits:

- It will facilitate knowledge transfer and contribute to local capacity building;
- It will enable the company to jointly  participate on international bid thereby saving foreign currency;
- It will pave the way for the company to compete internationally in other countries thereby generating foreign currency to the nation.

## የማይጸብሪ-ዲማ ፕሮጀክት መዝግያ አውደ ጥናት

የማይፀብሪ-ዲማ ፕሮጀክትን መጠናቀቅ ምክንያት በማድረግ እና በፕሮጀክቱ ሂደት ያጋጠሙ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን ለመለየት ለሌሎች ፕሮጀክቶች መማሪያ እንዲሆን እና የፕሮጀክቱን አፈጻጸም መዝግቦ መያዝ እንዲያስችል የተዘጋጀ ወርክ ሾፕ በበሻሌ ሆቴል እ.ኤ.አ ግንቦት 8 ቀን 2013 ለግማሽ ቀን ተካሂዷል፡፡

በተዘጋጀው መርሃ ግብር መሠረት ስለ ፕግራሙ አጭር ማብራሪያ ከተሰጠ በኋላ ከሥራ ሂደት አንጻር በፕሮጀክቱ ከታች በተዘረዘሩት ነጥቦች ላይ በአፈጻጸም ላይ ግምገማ የተካሄደ ሲሆን በየመሃሉ ውይይቶች ተደርገዋል፡፡

- የፕሮጀክቱ  አደረጃጀት
- ከደንበኞች/Clients/ ጋር የነበረው ግንኙነት
- የፕሮጀክቱ ሪፖርት ይዘትና አቀራረብ
- የመሣሪያዎች እና ማሽኖች አጠቃቀም
- የሰው ሃብት አጠቃቀም
- የፕሮጀክት ግዥና አቅርቦት እንዲሁም
- የለውጥ ሂደት አስተዳደር ናቸው፡፡

በአጠቃላይ በውይይት የተነሱ ዋና ዋና ነጥቦች ላይ የጋራ መግባባት ላይ ከተደረሰ በኋላ በአሁኑ ወቅት በሥራ ላይ ያሉም ሆነ በቅርቡ የሚጀመሩ ፕሮጀክቶች ከማይፀብሪ-ዲማ ፕሮጀክት አፈጻጸም የታዮ በጎ ጎኖችን በማጎልበት እና የታዩ ድክመቶች እንዳይደገሙ ጥረት እንዲያደረጉ በማሳሰብ የፕሮግራም ፍጻሜ ሆኗል፡፡

## Maytsebri- Dima Project Closure Workshop

Following the completion Maytsebri- Dima Project, a half day closure workshop  was held on 8 May 2013 at Beshale Hotel to discuss on   problems encountered, strengths and weaknesses identified and to draw lessons of experience from the process. The major points of discussion on which evaluations were made include the following:

- Organization of the project
- Relations with the Client
- Content and presentation of reports
- Utilization of machinery and equipment
- Deployment of human resources
- Purchase and supply of project inputs
- Change management during the construction works

Intensive discussions were held on each of the above indicated issues following which it was concluded that the on-going projects should be able to enhance the success achieved during the construction works of the Maytsebri- Dima Project.





የማይፀብሪ-ዲማ ፕሮጀክት መዝጊያ አውደ ጥናት ሲካሄድ

**During Maytsebri–Dima Project Closure Workshop**

## የፕሮጀክት ሠራተኞች ስለኩባንያው ምን ይላሉ

የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ከማይፀብሪ- ዲማ - ፍየል ውሃ - አቢ አዲ - ሀውዜን ከሚያስገነባቸው መንገዶች ሁለቱን ለገምሹ በየነ ኮንስትራክሽን የሰጠ ሲሆን የመጀመሪያውን ፕሮጀክት ማይፀብሪ-ዲማ 76.6 ኪ.ሜ ሰርቶ ያጠናቀቀ ሲሆን ተከታዩን ፕሮጀክት ዲማ- ፊየል ውሃ 86 ኪ.ሜ እየሰራ ይገኛል፡፡ የመጀመሪያውም ማለትም ማይፀብሪ-ዲማ ፕሮጀክትን ከታቀደለት የጊዜ ገደብ ቀድሞ አጠናቋል፡፡ ይህም ለወደፊቱ ያገራችን የስራ ተቋራጮች ከውጭ ኩባንያዎች ባልተናነሰ ፕሮጀክቶችን ተረክበው በጥራት መስራት እንደሚችሉ ያመላክታል፡፡

ድርጅቱ ሁለተኛውን ፕሮጀክት (ዲማ-ፊየል ውሃ ፕሮጀክት) በጥራት እና በፍጥነት በታቀደለት የግዜ ገደብ እየሰራ ይገኛል፡፡ በዚሁ መሠረት የስራውን እንቅስቃሴና ስለኩባንያው አጠቃላይ ሁኔታ ከሦስት የፕሮጀክት ሠራተኞች ጋር ቃለ ምልልስ አድርገናል፡፡ ቃለ-ምልልሱ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡



ኢንጂነር አበራ መርጋ
በዲማ- ፊየል ውሃ መንገድ ስራ ፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ / Eng. Abera Merga, Dima– Feyel Wuha Road Project Manager

ኢንጂነር አበራ መርጋ በስቪል ምህንድስና የቢ.ኤስ ሲ ድግሪ ያላቸው ሲሆን በሙያ መስኩ ከ7 ዓመት በላይ ልምድ አለቸው

በመጀመሪያ ደረጃ ለቃለመጠየቅ ስለተባበርከን በጣም እናመሰግናለን

**ጥያቀ፡-** አስኪ ሥራ አስኪየጅነት ይዞት የሚመጣውን የስራ ጫና ቆራጥነት ጭካኔውሳኔ ሰጭነት እንዴት ይገልፁታል?

**መልስ** የፕሮጀክት ስራ አስኪያጅ ስትሆን ያለብህ ሃፊነት ከባድ ነው፡፡ ሁሉም ነገር ከአንተ ይጠበቃል ነገሮችን የማየት አድማስህ ሰፊ መሆን አለበት ከመወሰንህ በፊት በሁለት ተቃራኒ አቅጣጫ ቆም ብለህ ማሰብ አለብህ ፡፡ ከውሳኔህ በኋላ ስህተት ሆነ ትክክል ውሳኔህን ለማስፈፀም ቆራጥነት ይጠይቃል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ሃላፊነት ጭካኔን ይጠይቃል፡፡ ይኽ ማለት ሰብአዊነት አይሰማህም ማለት አይደለም፡፡ የሰራተኛው ህመም ይሰማሃል የፕሮጀክትህ ስራ ህመምም እንደዚሁ፡፡ በመሆኑም ውሳኔ መስጠት ብዙዎቹ ከሩቅ እንደሚያዩት ቀላል አይደለም፡፡

## Staff Reflection from Project Sites

The Ethiopian Roads Authority awarded two of the contracts for construction of road from Maitseberi–Dima-Feyel Wuha–Abi Adi-Hawazen to Gemeshu Beyene Construction PLC. The company has already completed one of the projects (Maitseberi–Dima 76.6 km road) ahead of the schedule. This shows that local companies have the potential to replace the role currently played by foreign companies.

The second project (Dima-Feyel Wuha 86 km road project) is currently on-going as per its schedule. We have interviewed three of our project staff for their reflection on the company and on-going projects.

Eng. Abera Merga holds BSC degree in Civil Engineering and has over 7years of experience in his field of specialization. He worked in various capacities including office and site engineer, office and project engineer, operational engineer, and construction engineer.

**Q.** *Currently you are a manager of the Dima-Feyel Wuha Road Project. Could you tell me the challenges with being a manager in terms of workload, commitment, determination and d e - cision making such responsibility entails?*

**Res.** *The responsibilities of a project manager are complex. You need to look at issues from different perspectives before passing decisions. Determination is required to ensure that your decisions are executed irrespective of whether the decision is found to be right or wrong. But it does not mean that you can ignore humanity issues. You feel the pain of the employees and also the pain of the project you manage. Hence decision giving is not an easy task.*

**ጥያቀ፡-** የድርጅቱ እሴቶች እንዴት ታያለህ?

**መልስ፡-** የገበኮን እሴቶች ብዙ ናቸው፡፡ አንዳንዶቹን በመጥቀስ ድርጅቱ ሰራተኛን ከታች ጀምሮ የመያዝና የማሳደግ የማብቃት ባህል አለው፡፡ ድርጅቱ የስራ ጥራት፣ በጊዜ አጠቃቀም የፕሮጀክቱን የልብ ትርታ የማዳመጥ፣ መልካም የሆኑ ተሞክሮዎችን ስራ ላይ በማዋል ጠንካራ ነው፡፡ ሁሉም የድርጅቱ ሰራተኞች በየኔነት ስሜት የሚሰሩ እና ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልጉ አቅርቦቶች በፍጥነት ወደ ፕሮጀክት መላካቸው ሊጠቀሱ የሚችሉ እሴቶች ናቸው፡፡

**ጥያቀ፡-** በድርጅቱ ፕሮጀክቶች መካከል ያለው ግኑኝነት ምን ይመስላል?

**መልስ፡-** ድርጅታችን በአሁኑ ሰዓት አራት ፕሮጀክቶች አሉት በፕሮጀክታችን መካከል ያለው ግንኙነት እስካሁን በነበረው የማይፀብሪ ዲማ እና ዲማ-ፍየል ውሃ ፕሮጀክት ተከታታይ ፕሮጀክት እንደመሆናቸው በመረዳዳት እና በመደጋገፍ የማይፀብሪ-ዲማ ፕሮጀክት ከተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ በፊት ማስረከብ ተችሏል፡፡ በቀጣይ ድርጅቱ ያሰበው የፕሮጀክቶች የእርስ በእርስ ልምድ ልውውጥ ፕሮግራም በ2006ዓ.ም ተግባራዊ ይሆናል ብዬ አስባለሁ፡፡

**ጥያቀ፡-** በአለም አቀፍ እና በአገር አቀፍ ደረጃ የገበኮን ደንበኞች እና የሰራተኞች ምርጫ ለማድረግ ድርጅቱ ምን መስራት አለበት ብሎ ያሚናሉ?

**መልስ፡-** በደንበኞች እና በሰራተኞች ዘንድ ቁጥር አንድ ተመራጭ ለመሆን ድርጅታችን ብዙ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል፡፡ ለምሳሌም ዘመናዊ አሰራርን ለመከተል ISO 9001: 2008 ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል፡፡ የተለያዩ መልካም ተሞክሮዎችንም ከፍተኛ ባለሙያዎችን በአማካሪነት ቀጥሮ እያሰራ ይገኛል፡፡

**ጥያቀ፡-** ድርጅቱ ሠራተኞችን የማብቃት ሥራ እንዴት ነው? ከዚህም በፊት ምን ተሰራ ? ለወደፊትስ ምን ታስቧል?

**መልስ፡-** ድርጅታችን ማንኛውንም ሰራተኛ በሚሰራው ስራ የላቀ እውቀት እንዲኖረው ይፈልጋል፡፡ ለዚህም የተለያዩ ስልጠናዎችን ለሰራተኞቹ ይሰጣል ያዘጋጃል፡፡ ‹‹ Manual ›› መሰረት ማኛውንም ሰራተኛ የሙያ ማሻሻያ ስልጠና ለመስጠት በጀት ተይዟል፡፡

**ጥያቀ፡-** የሠራተኞችን አያያዝ በተመለከተ?

**መልስ፡-** የተሰራተኛን አያያዝ በተመለከተ ድረጅታችን በመልካም ስማቸው ከሚጠሩ ድርጅቶች አንዱ ነው፡፡ መስተካከል ያለበት እና መሻሻል ያለበት ስራ ደግሞ የሰራተኛን አስተያየት መሰረት አደርጎ እየተሰራ ነው፡፡

**ጥያቀ፡-** የዚህ ፕሮጀክት የምርቃት ቀን አሊያም ወር ይገምቱ?

**መልስ፡-** የዲማ -ፍየል ውሃ ፕሮጀክት ምርቃት በተያዘለት ጊዜ በፊት እንደሚሆን በጣም እርግጠኛ ነኝ ፡፡ የመጀመሪያውን 40 ኪ.ሜ (አርባ) ኪ.ሜ ታህሳስ 2006ዓ.ም ላይ እናስረክባለን ቀሪውን ደግሞ የካቲት 2007ዓ.ም ከፕሮጀክቱ ማብቂያ 6 ወር በፊት እንጨርሳለን ብዬ አምናለሁ፡፡

ግዜህን ሰጥተህ ለቃለ መጠየቅ ስለ ተባበርከን እናመሰግናለን፡፡

**Q.** How do you see the values of the company?

**Res.** GEBECON has so many values. It has the culture of nurturing and upgrading its employees. The company is strong in maintaining quality of works, efficient utilization of time, follow-up of projects and use of best practices. The sense of belongingness of the employees and timely delivery of supplies to the project sites can be mentioned as some of the good values of the company.

***Q.*** *How do you evaluate the relationship between sister projects?*

***Res.*** *Currently our company has four projects. As observed in the case of Maytsebri- Dima and Dima-Feyel Wuha projects, there is good relationship and sense of supporting each other. That is one of the reasons for completion of the Maytsebri-Dima project ahead of the schedule. We hope to maintain such cooperation and sharing of experience in the future.*

***Q.*** *What are the measures being taken by* GEBECON to be the first choice by its clients and employees? What are measures to be taken in the future?

***Res.*** *The company is taking various measures to be the first choice by its clients and employees. For instance it is implementing the* ISO 9001: 2008 and employing highly qualified consultants to obtain lessons on best practices.

***Q.*** *What about building the capacity of employees? What are measures taken so far? And what need to be taken in the future?*

***Res.*** *The company committed to enhance the skill and competence of its employees. To this end it is providing various type of training and allocates budget for skill upgrading trainings.*

***Q.*** *How about handling of employees?*

***Res.*** *The company is one of the companies known for better handling of employees. It duly considers the opinion and comments of employees on issues that need to be improved with respect to employees handling.*

***Q.*** *When do you think this project will be inaugurated?*

***Res.*** *I am quite sure the inauguration of the Dima-Feyel Wuha project will be ahead of the set schedule. We will surely handover the first 40 km by the coming December 2013. The remaining portion will be completed by February 2015, that is six months ahead of the schedule.*



ኢንጂነር ተስፋዬ አበበ
የ አዘዞ ጎርጎራ መንገድ ፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ
Eng. Tesfaye Abebe, Azezo Gorgora Road Project Manager

የመንገድ ሥራ ከፍተኛ የሆነ የመሳሪያ የሰውና የማቴሪያል ግብዐቶች የሚጠይቅ ዘርፍ እንደመሆኑ መጠን በእቅድና በጥንቃቄ የሚከናወን መሆን ይጠበቅበታል፡፡ ከመሳሪያ አቅርቦት ጋር በተያያዘ መሳሪያውን ከማቀረብ ጎን ለጎን ከሚጠይቀው የሰለጠነ የሰው ኃይል ጋር ወቅታዊ የሆነ የመለዋወጫ ዕቃ አቅርቦት ቅንጅትና ክትትል ወሳኝ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ተፈላጊውን የሰው ኃይልና የኮንሰትራክሽን እቃዎች በወቅቱና በተገቢው ጊዜ በማደርስ ስራው ተያይዞ ያለማቋረጥ እነዲቀጥል ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ይህም ከፍተኛ የሆነ የፋይናንስ አቅምና የአስተዳደር ዘዴ ስርአቱንም ጭምር የመዘርጋትና የመከታተልን ሀላፊነት ይጠይቃል፡፡ እነዚህና ሌሎችም በኮንስትራክሽኑ ውስጥ የሚያጋጥሙ ሁኔታዎች ተዳምረው ሥራውን ውስብስብ የሚያደርጉት ሲሆን ገበኮን ይኸንን በማሳከት የተዋጣለት የኮነሰትራክሽን ድርጅት ነው፡፡

*ኢንጂነር ተሰፋዬ በሲቢል ምህንድስና የቢ.ኤስ.ሲ ድግሪ አላቸው፡፡ በመንገድ ኮንስትራክሽን ዘርፍ ከ21 ዓመት በላይ ልምድ ሲኖራቸው የፕሮጀክት መሃንዲስ፤ የፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅና የዲስትሪክት ሥራ አስኪያጅ በመሆን ሠርተዋል፡፡*

Since the construction of roads requires enormous inputs of human, materials and financial resources, it needs meticulous planning. Close co-ordination has to be maintained in the supply of the inputs including spare parts for construction machinery and equipment. This inturn entails mobilization of huge financial resources, efficient and effective management system and close follow-up. These and other unforseen factors make undertaking of construction activities a complex task. GEBECON in this regard has proved to be a successful company in meeting the challenges of undertaking construction projects.

*Eng. Tesfaye Abebe holds BSC degree in Civil Engineering. He has over 21 years of experience in road construction sector and worked as project engineer, project manager, and district manager..*



ኢንጂነር ማንደፍሮ በርሁን
የመሃል ሜዳ-ዓለም ከተማ መንገድ ፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ
Eng. Mandefro Berihun, MehalMeda-Alem Ketema Road Project Manager

ለሥራ ከፍተኛ ተነሳሽነትና ፍላጎት ካላቸው የዚህ ፕሮጀክት ቡድን አባላትና በዋና መ/ቤት ከሚገኙ የኩባንያው ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ጋር ለመሥራት በመቻሌ ከፍተኛ ደስታ ይሰመኛል፡፡ገበኮን የሚሠራቸውን ፕሮጀክቶች ከተያዘለት ፕሮግራም ቀደም ብሎ በማጠናቀቅ እስከሁን ባሳየው የለቀ አፈጻጸም ከፍተኛ ዝናና እውቅና ለማግኘት በቅቷል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በእጃችን የሚገኙትን ፕሮጀክቶች ከኮንትራት ጊዜአቸው ቀደም ብለን በማጠናቀቅ የኩባንያውን መልካም ስም የበለጠ ለማሳደግ ተግተን መሥራት ይጠበቅብናል፡፡

*ኢንጂነር ማንደፍሮ በስቨል ምህንድስና የቢ.ኤስ ሲ ድግሪ ያላቸው ሲሆን በመንገድ ግንባታ ሥራ ዘርፍ በተለያዩ ድርጅቶች ውስጥ ከአሥር ዓመት በላይ አገልግለዋል፡፡.*

I am very happy to work with highly motivated project team and support staff at the head office who are committed to their duties. GEBECON has already built strong reputations through its extraordinary performance of accomplishing project works ahead of schedule.

I and on behalf of my team in the project site, I would like to wish fruitful success to our company. I hope all members of the company keep on working hard in order to complete the project works at hand before the stipulated contract time.

*Eng. Mandefro holds BSC degree in Civil Engineering. He has over ten years of experience in road construction sector including project engineer, officer engineer, design and implementation team leader, and district engineer division manager.*



ኢንጂነር ቢንያም ውብሸት
የሐረር ባይፓስ መንገድ ፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ
Eng. Benyam Wubishet, Harar By-Pass Road Project Manager

ገበኮን ኩባንያ  እንደድርጅት የራሱ የሆነ በርካታ ልዩነቶች አሉት፡፡ የጠበቀ የሥራ ፍሰት ሥርዓት ያለው መሆኑ፤የሥራ ሥነ ምግባሩና ባህሉ፤የISO 9001:2008 ጥራት አስተዳደር ሠርትፊኬት ለማግኘት  የሚያደርገው ጥረት  ከሚጠቀሱት ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ናቸው በመሆኑም ከዚህ ዓይነቱ ኩባንያ ጋር ለመሥራት በመቻሌ ከፍተኛ ደስታ ይሰመኛል፡፡

*ኢንጂነር ቢንያም በስቪል ምህንድስና የቢ.ኤስ ሲ ድግሪ በከተማ አስተዳደር ዲፕሎማ አላቸው፡፡ በእነዚህ የሙያ መስኮች በተለያዩ መንግሥታዊ መ/ቤቶችና የግል ድርጅቶች በመሥራት ከ13 ዓመት በላይ የሥራ ልምድ አላቸው፡፡*

It is my deepest impression that GEBECON has many unique qualities. These include its strict work-flow, work ethics  and culture as well as its endeavors to become ISO certified.  I am very much delighted to be part of this commendable staff.

*Eng. Benyam  holds BSc in Civil Engineering and post-graduate Diploma in Urban Management. He has over 13 years of experience working in government offices and private contractors in various managerial positions. He had served as Dire Dawa Roads Authority G/Manager for more than nine years. He participated in Dire Dawa administration road design, construction, and maintenance/both in gravel and asphalt roads. He is the one who has pioneered the technology of cobble stone for Ethiopia for the first time.*



አቶ ሰሎሞን ወልዴ/Solomon Wolde
የከባድ መኪና ሹፌር/Heavy Duty Driver

በመጀመሪያ ደረጃ ለቃለ መጠየቅ ስለተባበርከን በጣም እናመሰግናለን

**ጥያቀ፡-** ራስህን አስተዋውቅልኝ፡፡

**መልስ፡-** ስሜ ሰለሞን ወልዴ ይባላል በገበኮን የከባድ መኪና ሹፌር ነኝ

**ጥያቀ፡-**መቼ ድርጅቱን ተቀላቀልክ?

**መልስ፡-** በ2001 ዓ.ም

**ጥያቀ፡-** ስራ ስትጀምር በምን የስራ ዘርፍ ነው ስራ የጀመርከው?

**መልስ፡-** ስራ የጀመርኩት በቀላል መኪና ሹፌርነት ሲሆን በድሬዳዋ ደንገጐ የመንገድ ጥገና ሥራ ፕሮጀክት ነው፡፡

**ጥያቀ፡-** ሥራ ስትጀምር ደመወዝህ ስንት ነበር

**መልስ፡-** ስድስት መቶ አንድ ብር (601)

**ጥያቀ፡-** ዛሬስ

**ጥያቀ፡-** ከታክስ ውጪ አበልና ደመወዜ አምስት ሺ ሶስት መቶ (5,300) ብር ነው

ይህ ማለት ዛሬ ከመጀመሪያው ስናነፃፅር እድገቱ በዘጠኝ እጥፍ ይሆናል ማለት ነው፡፡

**መልስ፡-** አዎ! በሚገባ!

**ጥያቀ፡-** ድርጅቱን ስትቀላቀል እና በዛሬ መካከል ያለው ልዩነት ምን ይመስላል

**መልስ፡-** ዋው! ኧረ በጣም በጣም ልዩነት አለው፡፡ ልዩነቶቹ በብዙ ነገር ከፍለን ማየት እንችላለን፡፡ ለአብነት የሰው ሃይል ስንመለከት ያኔ ትንሽ ነበረ ዛሬ ግን እንደሚታየው በዚህ ፕሮጀክት ብቻ ግዚያዊ ሰራተኛ ራሱ ከአንድ ሺ በላይ ነው፡፡ቋሚ ሰራተኛ ደግሞ ወደ 280 ይሆናል ስለዚህ ልዩነቱ ሰፊ ነው በሌላ በኩል ስንመለከት ያኔ የነበሩ መኪኖች እና ማሽኖች የተወሰኑ ናቸው ዛሬ ግን በጣም ብዙ ማሽን እና መኪኖች ናቸው እየሰሩ ያሉት፡፡ በአጠቃላይ ድርጅቱ እድገቱ አሰደሳችና አስደናቂ ነው፡፡ ጐን ለጐን በዚህ መጠን ሠራተኞችን እያደጉ እየተለወጡ ይገኛሉ፡፡ ይህ ማለት ደግሞ የድርጅቱ እድገት በሁሉም ዘርፍ ነው፡፡

**ጥያቀ፡-** ድርጅቱ ባለውለታዬ ነው ብለህ ታስባለህ?

**መልስ፡-** አዎ! ምክንያቱም ከትንሽ መኪና ወደ ትልቅ መኪና አሳድጐኛል፡፡ ደመወዜም በዛው መጠን አድጓል፡፡በማገኘው ጥቅማ ጥቅምም ራሴንና ቤተሰቦቼን እየረዳሁ እገኛለሁ፡፡ በተጨማሪም በነፃነት የምሰራበት ድርጅት ስለሆነ ለኔ ባለ ውለታዬ ነው፡፡

**ጥያቀ፡-** የስራ ትጋትህ ምን ይመስላል?

**መልስ፡-** ያለኝን አቅም ሳልቆጥብ ለጉልበቴ ሳልሳሳ እየሰራሁ እገኛለሁ፡፡ ለዚህ ደግሞ ምስክሬ እየተሰራ ያለውን ሥራ ማየት በቂ ነው፡፡

**ጥያቀ፡-** የድርጅቱ ባለውለታ መኪና /ማሽን

Thank you for your cooperation for this interview.

Q. Could you introduce yourself please?

Res. My name is Solomon Wolde, I am a driver of heavy truck at GEBECON

Q. When did you join GEBECON?

Res. In 2001 E.C

Q. What was the field of work you were assigned to up on joining GEBECON?

Res. I commenced works as driver of light vehicle at the Dire Dawa-Dangago Road Maintenance Project of the company.

Q. How much was your salary at the time?

Res. My salary at the time was Birr 601.

Q. How much is your current salary?

Res. My current income (salary and perdiem other than tax) is Birr 5,300.

Q. That is your income increased by nine fold?

Res. Yes

Q. How do you compare the difference?

Res. The difference is enormous. There are so many changes in the company. For instance when I was employed, the human resource of the company is few. Today we have more than 1000 temporary and 280 permanent employees for this project alone. The number of construction machinery and heavy vehicles also significantly increased. So the company is witnessing enormous growth in all aspects.

Q. Do you think GEBECON made you a favor?

Res. Yes, it has promoted me from light vehicle driver to position of heavy truck driver. It has increased my salary so thant I can comfortably support my self and my family. I have also full freedom in the company. All these are the favours the company made for me.
are testimony for this.

Q. What extra effort do you make on your duty?

Res. I exert all efforts possible to accomplish my duty. The results of the works done are testimony for this.

Q. Is there a vehicle or machinery you consider as having special contribution for the company?

**መልስ፡-** ረጅም ሳቅ ቂቂቂ…ካ ካ ካ ካ … በህሊናዬ ወደኋለኛው ዓመት ስመለስ አንድ አስደናቂ ዛሬም ድረስ ያለች ደብል ጋቢና ቶዮታ መኪና አለች፡፡ ቅፅል ስሟ ሉሲ ትባላለች፡፡ የምን ጊዜም የድርጅቱ ባለ ውለታ ነች፡፡ እስከ ዛሬ ድረስ ሰለቸኝ ደከመኝ ሳትል የዶዘሮችን እስትንፋስ ይዛ ያለች መኪና ናት፡፡ ሉሲ ዕድሜዋ ረጅም ነው ለመስራት ብዙ ምክንያት አታቀርብም፣ በመቆምም አትታማም፣ ካሉት መኪኖች በዘላቂነት ተራሮች ሳይበግሯት የስራ ድርሻዋን ትወጣለች፡፡ በሉሲ የመጣ በግርማ (ከባድ ማሽን መካኒክ) አይን የመጣ ነው፡፡ ሁለተኛዋ ደግሞ ሶሬቲ ትባላለች ኤክስካቫተር ስትሆን አሷም የድርጅቱ ባለ ውለታ ነች፡

ግዜህን ሰጥተህ ለቃለ መጠየቅ ስለ ተባበርከን አናመሰግናለን፡፡

**መልስ፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡



አቶ ጌቱ አለሙ/Getu Alemu
የከባድ መኪና የነዳጅ ቦቴ ሹፌር /Fuel Truck Driver

በመጀመሪያ ደረጃ ቃለመጠየቅ ለማድረግ ስለተባበርከን በጣም እናመሰግናለን

**ጥያቄ፡-** ራስህን አስተዋውቅልኝ?

**መልስ፡-** ጌቱ አለሙ አባላለሁ በገበኮን የከባድ መኪና የነዳጅ ቦቴ ሹፌር ነኝ

**ጥያቄ፡-** መቼ ድርጅቱን ተቀላቀልክ

**መልስ፡-** በ1995 ዓ.ም

**ጥያቄ፡-** ስራህን ስትጀምር በምን የስራ ዘርፍ ነው ስራ የጀመርከው

**መልስ፡-** ስራ የጀመርኩት በረዳት ሹፌርነት ነው

**ጥያቄ፡-** ሥራ ስትጀምር ደመወዝህ ስንት ነበር

**መልስ፡-** አንድ መቶ ዘጠና ብር እና ሃያ ብር አበል ነው ሁለቱም ሲደመር ሰባት መቶ ዘጠና ብር ይመጣል

**ጥያቄ፡-** ዛሬስ

ከታክስ ውጪ አበልና ደመወዜ ስድስት ሺ ስምንት መቶ ብር ነው፡፡

**ጥያቄ፡-** ይህ ማለት ዛሬ ከመጀመሪያው ሲናነፃፀር እድገቱ 860% ይሆናል ማለት ነዋ

**መልስ፡-** አዎ! በሚገባ!

Q. Res. Hhhh… laughter. I remember one double cabin pick up Toyota. This car had a nick name called Lucy. Lucy is still serving. While other automobiles stop owing to different technical problems, Lucy serve without much problem even under difficult road condition. This car has contributed much to the company. The second was excavator which is nicknamed as Soreti which served for longer time and is still serving the company.

Q. Thank you for the interview.

Res. Thank you

Q. Thank you for the interview and could you Introduce yourself please?

Res. My name is Getu Alemu, I am a driver of heavy truck of fuel tank in GEBECON

Q. When did you join GEBECON?

Res. In 1995 E.C.

Q. What was your job position when you joined GEBECON?

Res. I was assistant driver.

Q. How much was your salary up on joining GBECON?

Res. My monthly salary was Birr 180 plus Birr 20 per diem, that is Birr 790.

Q. What about your current salary?

Res. My income (salary and per-diem other than tax) is now Birr 6,800.

Q. That means your income has increased by 860%

Res. Yes.

Remember that success is not the high position you will get in your life time, it is not the repute or good name you have among other men, simply success is the faithful part of your works which you have been doing in your life time. **(George Washington)**

**ጥያቀ፡-** ድርጅቱን ስትቀላቀል እና በዛሬ መካከል ያለው ልዩነት ምን ይመስላል

**መልስ፡-** ያኔ ስራውን የምንሰራ በራሳችን ነው፡፡ ጐሚስታ የለንም ኑሮም ከባድ ነበር፡፡ ያኔ የነበሩ ሰራተኞች ዋጋ ከፍለዋል፡፡ የድርጅቱ አቅምም ውሱን ነበር፡፡ መኪኖች እንደ ዛሬ አልበዙም ነበር፡፡ ነገር ግን ያኔም የስራ ወኔ የድርጅቱ የስራ ቅልጥፍና እንደ ዛሬ ከፍተኛ ነበር፡፡ ከአመት አመት እድገቱ እየቀጠለ የሰራተኛውም የመስራት ፍላጐት እና ችሎታ በጣም እያደገ መጣ፡፡ የነዚህ ሁሉ ውጤት ደግሞ ዛሬ የሚታየውን ገበኮን ወልደዋል፡፡ ነገ ደግሞ አስደናቂው አለም አቀፍ ገበኮን ይፈጠራል፡፡ ለዚህም ሙሉ እምነት አለኝ፡፡

**ጥያቀ፡-** ድርጅቱ ባለውለታዬ ነው ብለህ ታስባለህ?

**መልስ፡-** አዎ! ምክንያቱም በድርጅቱ ብዙ ነግር አግኝቻለሁ፡፡ ከረዳት የገልባጭ መኪና ሹፌር ወደ ገልባጭ መኪና ሾፌር ብሎም ዛሬ የነዳጅ ቦቴ ሹፌር ለመሆን ችያለሁ፡፡ በድርጅቱ ውስጥ የወረቅ ተሸላሚ ሰራተኛ ነኝ፡፡ ቅድም እንደነገርኩህ ደመወዜ ከ 790 ወደ 6800 ብር አከባቢ ደርሷል፡፡ ስለሆነም ድርጅቱ ከፍዬ የማልጨርሰው ውለታ አለብኝ፡፡

**ጥያቀ፡-** የስራ ትጋትህ ምን ይመስላል?

**መልስ፡-** ይህን አስቲ ላንተ ልተውልህ ከመጣህ በሃላ እንዴት እየሰራሁ እንደሆነ ታውቀዋለህ፡፡ ስሰራ ምን ሊሆን ፡እንዴት ልናድግ እንደምንችል ከገበኮን ትምህርት ቤት ተምሬአለሁ ፡፡ ስለሆነም የማልተጋበት ምክንያት የለም፡፡ ለኔም በገበኮን ለማመን እና አብሮ ለመስራት ብዙ ተነግሮ የማያልቅ ምክንያቶች አሉኝ፡፡ ስለሆነም ትጋት የድርጅታችን መሪ ቃል ነው፡፡ የኔም የህይወት ስንቅ ነው፡፡

**ጥያቀ፡-** ድርጅቱን የበለጠ ለማሳደግ ብሎም አለም አቀፍ ካምፓኒ ለማድረግ ከሰራተኛ እና ካሰሪው ምን ይጠበቃል?

**መልስ፡-** ከሰራተኛ፡- ቀን ከለሊት ሥራው የኔ ነው ብሎ የስራ ሰዓቱን አንድም ደቂቃ ሳይባክን ስራውን መስራት አለበት፡፡ ውጤት ተኮር የሆነ ሥራ መስራት አለበት፡፡

ከአሰሪው ደግሞ ጥሩ አመራር ተባብረን ተከባብረን ተያይዘን ሊያሰራ የሚችል ዕቅድ አዋጪ የሆነ ስልት እስትራቴጂ መንደፍና ለተግባርነቱ የሚተጋ ሰርቶ የሚያሰራ አሰሪ መኖር አለበት፡፡

**ጥያቀ፡-** የድርጅቱ በለውለታ መኪና /ማሽን

**መልስ፡-** ለኔ የድርጅቱ በለውለታ መኪና ቢጫው የአቶ ገብሬ ዳምትራክ እና የአቶ ግርማ ሉሲ ናቸው፡፡ እነሱ መቼም አይረሱኝም፡፡

**ጥያቀ፡-** መልዕክት ካሎት

**መልስ፡-** ከጅማሬ እስከዛሬ ድረስ ያለው ጥሩ ፍቅር መቀጠል አለበት፡፡ ፍቅራችን እና አንድነታችን ለዛሬ እድገታችንም ምክንያት ነበር ፡፡ አሁንም የበለጠ መቀጠል አለበት፡፡ የሰራተኛውም ሆነ የአሰሪው የስራ ፍቅር ምን ጊዜም መቀጠል አለበት፡፡ ሰራተኛው ለድርጅቱ ቋሚ እሴት ስለ ሆነ ጠንክሮ መቀጠል አለበት፡፡

**ጥያቀ፡-** ግዜህን ሰጥተህ ለቃለ መጠየቅ ስለ ተባበርከን እናመሰግናለን፡፡

**መልስ፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

Q. How do you see the difference between the time you joined the company and today?

Res. There is much difference. We used to repair tyre ourselves, because there was no tyre repair at that time. The capacity of the company at that time was limited. But today GEBECON grew significantly. It has so many machinery and heavy trucks. I am fully confident the company will be an internationally known company in the future.

Q. Do you think GEBECON made you a favor?

Res. Yes, it has promoted me from the position of assistant driver to driver of dump truck and know to driver of fuel tanker. I am also awarded gold medal for outstanding performance. My income has been increased from Birr 790 to Birr 6,800. Hence the company made me so many favors.

Q. What extra effort do you make on your duty?

Res. Let me leave this to you, because you have seen just how I am working. I have learned from GEBECON how to grow big. So making extra effort is our main value here in GEBECON.

Q. What is expected from the company and its employees for further growth to make GEBECON an internationally known company?

Res. The employees are required to work day and night without wasting time. We need to be result oriented in our activities. The company on its part should formulate feasible plans, strategies and put in place a more efficient system.

Q. What is the most memorable vehicle or machinery of the company in terms of their contribution?

Res. I think the yellow dump truck of Ato Gebere and Lucy of Ato Girma are the most memorable that served the company for long time.

Q. Any other message?

Res. We need to maintain the existing sense of cooperation and love among ourselves to keep up our performances.

Q. Thank you for the interview.

Res. Thank you.

- Never be discouraged by obstacles, difficulties and problems, make them a climbing step towards success. (**<u>Nelson Mandela)</u>**
- Be a person of action because action speaks out louder than words. **(Carl Bruce)**

## ለረጅም ጊዜ አገልግሎት እውቅና ስለመስጠት

ሠራተኞቹ በኩባንያው እንዲኮሩና ውጤታማ እንዲሆኑ ለማደፋፈር ኩባንያውን በታማኝነትና በቅንነት ላገለገሉ ሠራተኞቹ የእውቅና አሰጣጥ ሥርዓት ዘርግቷል፡፡ በዚሁ መሠረት በኩባንያው አሥር ዓመት ያገለገለ ሠራተኛ በይፋ እውቅና እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡ ሠረተኞች ለሚያበረክቱት የረጅም ዘመን አገልግሎት እውቅናና ሽልማት መስጠት የኩባንያው ፖሊሲ አካል ነው፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ  በተለያዩ ደረጃ የሚሠሩ ሠራተኞችና ቡድኖች በየዓመቱ ለሚያስመዘግቡት የላቀ ሥራ አፈጻጸም ኩባንያው እውቅናና ሽልማት ይሰጣል;; የዚህም እውቅናና ሽልማት ዓለማ ሠራተኞችና የሥራ ቡድኖች ከመደበኛ የሥራ ግዴታቸው በተጨማሪ በአዳዲስ ፈጠራና በሚያከናውኑት የሥራ ጥራት የላቀ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ለማበረታታት ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በኩባንያው ራዕይ በግልጽ እንደተቀመጠው ሠራተኞች ለኩባንያው ባበረከቱት አስተዋጾ መጠን የአክሲዮን ባለድርሻ የሚሆኑበት ሁኔታ እየተመቻቸ ነው፡፡ ይህም እርምጃ ሠራተኞች የበለጠ የባላቤትነት ስሜት ኖሯአቸው ለቀጣይ የኩባንያው ዕድገትና ስኬት ተግተው እንዲሠሩ እንደሚያበረታታቸው ይታመናል፡፡



የገበኮን ቲም በጥገና ወቅት/GEBECON TEAM During Maintenance

Better Keep yourself clean and bright, you are the window through which you must see the world. (George B. Shaw)

## Service Recognition and Award Program

In order to develop the culture of organizational pride and a climate of success, GEBECON Plc appreciates and recognizes the commitment, loyalty and faithful service of its employees. Each permanent employee will be officially honored on reaching ten years of service in his/her career at GEBECON Plc. Hence, it is the policy of GEBECON Plc to recognize the length of service through awards of honor to those employees who have demonstrated their commitment and loyalty towards GEBECON Plc.

Apart from this, GEBECON Plc appreciates and recognizes employees and teams at different levels for extraordinary performance and contribution towards the success of construction projects on yearly basis. The purpose of the award shall be to motivate employees and teams to go beyond the call of duty and run for innovative and quality driven performance solutions and thereby exceeding client expectations at all time.

Moreover, as clearly stipulated in its vision statement, GEBECON Plc will soon transform itself into a share company whereby employee shareholding scheme - in which employees own limited shares based on their commitment, loyalty and contribution to the company - becomes a reality. This is believed to boost exemplary performance, company belongingness and sense of collective ownership to guard the success and growth of the company in the years to come.

International Facts/Truth

- Five million people live on/ near/ straight around the world.
- Fifteen million feet print on the road every day around the world.
- Twenty eight thousand road accidents happen daily around the world.

## የገበኮን ራዕይ፤ ተልዕኮና እሴቶች

### ራዕይ

የገበኮን ራዕይ በኮንስትራክሽን ዘርፍ በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ያለውና ግንባር ቀደም ኩባንያ ሆኖ መገኘት ነው፡፡

### ተልዕኮ

ተልዕኮአችን ከፍተኛ የጥራት ደረጃ ያላቸው መንገዶችን በተመጣጣኝ ወጪና በኮንትራት መሠረት ሠርቶ በማስረከብ የደንበኞችንና የባለድርሻ አካላት ፍላጎት ማርካት ነው፡፡

ለተልዕኮአችን ስኬት ከሚንከተላቸው ስልቶች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ

- ዘመናዊ የኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም፤ጠንካራ የማኔጅመንት ሥርዓት መዘርጋትና የኩባንያው የፋይናንስ አቋም አስተማማኝ ማድረግ፣
- አዳዲስ ለውጦችን ከተወዳዳሪዎቹ ቀድሞ በጥራትና ቅልጥፍና ተግባራዊ በማድረግ
- የኩባንያውን የውስጥ አቅም በመገንባትና የተሻሻሉ የኮንስትራክሽን ማኔጀመንት ዘዴዎችን በመጠቀም ከአገር ውስጥና ከአገር ውጪ ታዋቂ ከሆኑ የኢንጂኔሪንግ ዲዛይንና ኮንስትራክሽን ኩባንያዎች ጋር ተባብሮ መሥራት፣
- የግንባታ ሥራዎች በተፈላገው ጥራትና ጊዜ እንዲጠናቀቁ አስተማማኝ አቅርቦት መኖሩን ለማረጋገጥ በግንባታ ማቴሪያሎች አቅርቦት ሥራ ውስጥ መግባት፣

### እሴቶች

- የሠራተኞች ተነሳሽነትና ቆይታ ማበረታታት
- የቡድን ስሜትና ምን ጊዜም የመማር ዝነባሌን ማሳደግ
- መልካም ባህሪያትን (ሐቀኝነት፤ታማኝነትና የደባሩ እውቀቶችን) ማበረታታትና በሞዴልነት መጠቀም፡
- የሠራተኞን ተሳትፎ ማሳደግ፤
- ከባለድርሻ አካላት ጋር ቀጠይነት ያለው ግኑኘነት ማዳበር፤
- ለውጦችን በመልካም አጋጣሚነት መውሰድ፤
- ግልጸኝነት፤ተጠያቂነትና የሙያ ሰነምግባር በኮንስትራክሽን ዘርፍ ማስፋፋት

## Vision, Mission and Values

### Vision

GEBECON PLC envisions growing into a share company so as to become an internationally reputable and leading company in the construction sector.

### Mission

Our mission is to meet the expectations of our clients and stakeholders by constructing high quality roads at reasonable cost and within the contract period.

To achieve our mission, we

- Put in place strong and modern construction management systems and technologies to grow into a financially sound construction company;
- Take a long term perspective by implementing important changes, more effectively and efficiently than our competitors, to improve the quality of road construction management in the country;
- Partner with renowned and important companies engaged in the area of engineering design and construction, local and overseas, as a strategy to build in-house capacity and facilitate the adoption of best construction management practices.;
- Engage in the business of construction related supplies to ensure reliability and delivery of construction works on time and within stated quality standards.

### Values

- Foster improved staff motivation & retention.
- Cultivate life-long learning and employee team spirit.
- Model and reward good behavior (honesty, loyalty, resourcefulness)
- Focus on staff to gain their full support and commitment
- Build & maintain synergy with stakeholders
- Embrace challenge as an opportunity
- Promote transparency, responsibility and professionalism in the construction sector

## ኢ.ሊ.ሊ. አንተርናሽናል ሆቴል—አዲሱ የገበኮን እህት

## Elilly International Hotel: The New GEBECON Sister Company



ዶ/ር አብዱሰላም ባሬንቶ፣ የአሊ.ሊ. ኢንተርናሽናል ሆቴል ማኔጅንግ ዳይሬክተር
Abdussellam Barento (PhD), Managing Director, Elilly International Hotel

ገበኮን የሥራ አድማሱን በማስፋፋት በሆቴል ኢንዱስትሪ ውስጥ ገብቷል፡፡ ገበኮን ኢ.ሊ.ሊ. ኢንተርናሽናል ሆቴል የተባለ ባለአምስት ኮከብ ዘመናዊ ሆቴል በመሃል አዲስ አበባ ያስገነባ ሲሆን ይህም ሆቴል ለእንግዶቹ ዘመናዊና ምቹ አገልግሎት በመስጠት አገራችን በእንግዳ ተቀባይነቷ ያላትን መልካም ስም የበለጠ በማጎልበት ረገድ አስተዋጾ እንደሚኖረው ይታመናል፡፡

የኢ.ሊ.ሊ. ኢንተርናሽናል ሆቴል መንትያ ህንጻዎች የተገነቡት በመሃል አዲስ አበባ ካዛንቺስ አካባቢ ወደ ተባባሩት መንግሥታት ስብሰባ ማዕከል በሚወስደው መንገድ ላይ ነው፡፡ ይህም አከባቢ ለከተማው የቢዝነስ ሥራዎች፤ ታሪካዊ ቦታዎች ፤ቤተመንግሥት፤ዋና ዋና የመንግሥት መ/ቤቶች፤የገበያ ማዕከሎች እምብርት በመሆኑ ለማንኛው ተጠቀሚ እንግዳ አመቺ ነው፡፡ ኢ.ሊ.ሊ. ኢንተርናሽናል ሆቴል ከቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ የሚርቀው በ3.8 ኪ.ሜ ብቻ ነው፡፡ የሆቴሉ እንግዶች ከሆቴሉ ህንጻ ላይ በመሆን አዲስ አበባን ከሁሉም አቅጣጫ ለማየት ይችላሉ፡፡ የቡና ቤቱና ምግብ ቤቱ ውብና ማራኪ ዲዛይን፤ ዓለም አቀፍ የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ ፋሲሊቲዎች፤ዘመናዊ የመሰብሰቢያ አደራሽና የመዋኛ ሥፍራዎቹ ጂምናዚየም ወ.ዘ.ተ ኢ.ሊ.ሊን በሆቴል ኢንዱስትሪው ተመራጭ ያደረጉታል፡፡

የኢ.ሊ.ሊ. ኢንተርናሽናል ሆቴል ተልዕኮ ዘመናዊ የሆቴል አገልግሎት በመስጠት እንግዶቹም ልዩነቱን እንዲያጣጥሙ ማድረግ ነው፡፡ የኢ.ሊ.ሊን ተልዕኮ ለማሳካት በምናደረገው ጥረት ባህላዊ እሴቶቻችንን ጠብቀን የእንግዶቻችንን፤ የሰራተኛውን፤ የሆቴሉን ባላቤቶችና ባለሀብቶች ፍላጎት ለማርካት ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል፡፡

When we want to talk about Elilly, the story will not be complete if we do not start from Gemeshu Beyene Construction (GEBECON) Plc . GEBECON gave birth to a sister company, a Five Star Hotel, in the heart of Addis Ababa, whose name is called Elilly International Hotel, which is bound to re-define modern hospitality in Ethiopia, for international travelers who expect right service at right price. Elilly is not an ordinary hotel as it is engineered by people who have passion for top-notch service and its service guide blue print that reflects its Brand.

Elilly International Hotel with its twin towers is situated in the heart of Addis Ababa, Kasanchis business district on the main entrance of the United Nations Conference Center (UNCC). It is ideally placed at a focal point between the city's business districts, historical landmarks, National Palace, major government offices & modern and traditional shopping centers. Ride to the Hotel only takes 3.8 KM from Bole International airport. The hotel offers breathtaking views from its rooms especially from the roof top Ellilly Bar & Restaurant where our guests take 360 degree view of the Capital City, Addis Ababa. The unique design of Bars, Restaurants, world class fitness facilities, swimming pool, conference and event venues with suitable and flexible set up puts Elilly on top of Hospitality Industry.

Elilly's mission is to provide authentic hospitality by making a difference in the lives of the people we touch every day.

ባለፉት አራት ዓመታት ሆቴሉ በግንባታ ላይ በነበረበት ጊዜ ለግንባታው መጠናቀቅ ከፍተኛ ጥረት ላደረጉ የገበኮን ሠራተኞች በሁሉም የኢሊሊ ባልደረቦች ስም ከፍተኛ ምስጋዬን አቀርባለሁ፡፡ አሁን ሆቴላችን ጉዞዋን ጀምራለች፤ ገበኮን እህት ኩባንያ አፈርቷል፡፡ እኛም በኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል ያለን ማኔጅመንትና ሠራተኞች የእህት የገበኮን ፈለግ ተከትለን ውጤታማ ሥራ እንደምንሠራ ሙሉ እምነታችን ነው፡፡



We focus on this mission in pursuit of our goal of becoming the most preferred brand in each segment that we serve for associates, guests, and owners/investors. We support our mission and goal by adhering to a set of core values that characterize our culture.

On behalf of all Elilly associates, I want to say to our big brothers, (GEBECON employees), who have worked tirelessly to support Elilly birth and nurtured it during the last four years, during its construction. Now Elilly is about to start its journey of Hospitality, as promised, to up lift the spirit of big brothers who hold us to high standard of ethics, always keeping you in mind that you have made us what we are today. We, at Elilly, will be test in action in the coming months. As we launch our contribution to Ethiopian hospitality and uphold the benchmark you have set for us, GEBECON on the move, now you have a sister company that emulates your role model and achievement. Thank you for the great job.



የአሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል የፊት ነስ ጅም ገጽታ

Elilly Fitness GYM Partial View